
3 ብር

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ

ቍጥር ፫

# የብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ




## ፩ኛ ዓመት የፓትርያርክነት በዓለ ሢመት መጽሔት

ግንቦት ፭ ቀን ፲፱፻፷፭ ዓ/

www.ethiopianorthodox.org

ይህ ሐዲስ ሕይወት የተባለው መጽሔት ለብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሁለተኛ ዓመት የፓትርያርክነት በዓለ ሢመት መታሰቢያ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ የስብከተ ወንጌልና የማስታወቂያ ክፍል ዋና መምሪያ ተዘጋጀ ።

www.ethiopianorthodox.org

# ማ ው ጫ

| ተራ ቍ. | አርእስት | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ | መግቢያ | ፲፩ |
| ፪ | መቅድም | ፲፫ |
| ፫ | ሥነ ሥርዓት ( ፕሮግራም ) | ፲፭ |
| ፬ | የጉባኤው ተሳታፊዎች | ፲፮ |
| ፭ | የበዓለ ሢመቱ አከባበር መግለጫ | ፳፫ |
| ፮ | ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ የሰጡት ቃለ በረከት | ፳፰ |
| ፯ | አስተዳደር | ፴፫ |
| ፰ | አንጻር አስተያየትና አጻፋው | ፴፬ |
| ፱ | ቤተ ክርስቲያን ምንሠራች ወይስ እኛ ምንሠራን | ፴፮ |
| ፲ | ለቤተ ክርስቲያን ምን ያስፈልጋል | ፴፱ |
| ፲፩ | ፍሬያማ የሆነ የጉባኤ ውይይት | ፵፩ |
| ፲፪ | ልማትና በልማት ተካፋይነት | ፵፭ |
| ፲፫ | የዐቢይ ጉባኤው ተከታታይ ጉባኤዎች | ፵፮ |
| ፲፬ | የቤተ ክርስቲያን ርምጃ | ፵፱ |
| ፲፭ | የንግግርና የመግለጫዎች አስተዋጽኦ | ፶ |
| ፲፮ | የጋዜጦች ሐተታና አርእስተ አንቀጾች | ፶፱ |

www.ethiopianorthodox.org



ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org



ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ
የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አልጋ ወራሽ።

www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org

# መ ግ ቢ ያ ፤

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሆነው የተሾሙበትን የሁለተኛውን ዓመት መታሰቢያ ስታከብር የተፈጸመውን የበዓል ሥነ ሥርዓት ለመግለጽ ለተዘጋጀው መጽሔት ይህ መግቢያ ተሰጠ ። በአንድ ቤት ውስጥ ያለውን ነገር መርምሮ ለማወቅ ወደ ውስጥ መግባት፤ወደ ውስጥ ለመግባትም በር ያስፈልገዋል።አንድ ዓይነት ጽሑፍ ለመመልከትና ሐሳቡን ለመረዳት ከጽሑፍ አስቀድሞ መግቢያ መስጠት ያስፈልጋል። መግቢያ ማለትም እንደ ዋዜማ ወደ መጽሐፉ ወይም ወደ መጽሔቱ ፍሬ ነገር ከመግባት አስቀድሞ መጽሐፍ የተጻፈበት ዓላማ አቅጣጫው ፤ (ሥነ ጽሕፈቱ) የሚታይበት ነው ።

፩ኛ/ የዚህ መጽሔት ዝግጅት ዓላማው የበዓሉን ሥነ ሥርዓት በሥነ ጽሕፈት ለትውልድ ለማስተላለፍና ለማሳየት ነው ።

፪ኛ/ አቅጣጫው ኢትዮጵያውያን ምእመናን ይህ መንፈሳዊ ክብር በነሱ እጅ ባልነበረበት ጊዜ የደረሰባቸውን ፤ የጐደለባቸውን ነገር ሁሉ አጉልቶ እያሰየ በእጃቸው በያዙት ጊዜ ደግሞ ምን ማድረግ ፤ በምን ዓይነት ጥንቃቄ መጠበቅ እንደሚገባቸው ለማመልከት ነው ።

፫ኛ/ ሥነ ጽሕፈቱ ፤ ሥነ ጽሕፈት የሚባለው ከመጽሐፍ ቅጽ ፤ ከፊደሉ አቀራረጽና አቀማመጥ ጀምሮ ፍሬ ነገሩ፤ አሠረ ምሥጢሩ ፤ ኃይለ ቃሉ ፤ በዐቢይ በንዑስ ምዕራፍ አከፋፈሉ ሳይቀር ግልጥ ብሎ የሚታይበት ነው ። ከዚህ በላይ ባሳየነው መሠረት በዚህ መጽሔት በቅዱስነታቸው በዓለ ሢመት የሁለተኛ ዓመት መታሰቢያ ሲከበር አስቀድሞ ከልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ጠ/ግዛቶችና አውራጃዎች፤አድባራትና ገዳማት የተውጣጡ ታላላቅ ሊቃውንት የተገኙበት ዐቢይ ጉባኤ መደረጉን በጉባኤው ላይም ይጠቅማሉ ተብሎ በታመነባቸው ልዩ ልዩ አርእስቶች ከጳጳሳት ፤ ከሊቃውንት ፤ ከካህናት ፤ ከምእመናን በተመረጡ ታላላቅ ምሁራን ንግግር መደረጉን፤በአርእስተ ነገሮቹ መሠረትም ሰፋ ያለ ውይይት መደረጉን በፍጻሜ በዓልም ጉባዔው የተወያየበት ሐሳብ በውሳኔ መልክ መውጣቱንና ወደሚያስፈልጉት ክፍሎች መተላለፉን በበዓሉ ዋዜማና በበዓሉ ዕለት የተገለጠውን ፍሬ ነገር የተፈጸመውን ግብር አጠቃሎ የሚያሳይ ሲሆን ይህን ዐቢይ ጉባኤ በመከተል የተፈጸሙትን የልዩ ልዩ ጉባኤያት ፍለጋም ያመለክታል ።

መቸም መግቢያ የሚያገለግለው ከውጭ ወደ ውስጥ ለመግባት ብቻ ነው ። አሁንም በዚህ መግቢያ ወደ መጽሔቱ ለመግባትና ወደ ፍሬ ነገሩ ለመድረስ ከቻልን ሐተታችንን በአጭሩ ዘግተን ወደ ፍሬ ነገሩ እንግባና የመጽሔቱን ይዞታ አንድ ባንድ እናስተውል ።

“ የጽድቅን በር ክፈቱልኝ ወደ ውስጥ ልግባና እግዚአብሔርን
ላመስግን ይህች በር የእግዚአብሔር ናት ጻድቃን ወደ እሷ ይገባሉ”

www.ethiopianorthodox.org

# መ ቅ ድ ም ።

የብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስን የሁለተኛ ዓመት የፓትሪያርክነት በዓለ ሢመት ምክንያት በማድረግ ከሚያዝያ ፳፫ ቀን ፲፱ ዓ/ም እስከ ሚያዝያ ፴ ቀን ፲፱ ዓ/ም ፯ ቀኖች ያህል የካህናት፤የሊቃውንትና የምእመናን ታላቅና የጋራ የሆነ ጉባኤ ተደርጎ ሰንብቷል ። ሰሞኑም የርክበ ካህናት ጉባኤ ጊዜ ስለነበረ ተባብሮ ተከብሯል ። በዚህም ጉባኤ ላይ ከጠ/ግዛቶችና ከአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት የመጡ ታላላቅ አበወምኔትና የአድባራ አለቆች ሲገኙ ጥሪ የተደረገላቸው የመንግሥትና የግል ድርጅቶች ሊቃውንት አስተናባሪዎችና አዘጋጆች የሆኑት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ጽ/ቤት ዓባሎች፤ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳት በልዩ ልዩ ዓበይት አርእስት ላይ ሰፋ ያለ ማብራሪያ በመስጠት ገለጻ አድርገዋል ። ከተወያዩባቸው አርእስቶችም ዋና ዋናዎቹ « ቤተ ክርስ ቲያንና ምእመናን ፤ ቤተ ክርስቲያንና ሥርዓቷ ፤ ቤተ ክርስታያንና ርምጃዋ» ሲሆኑ እነ ዚህንም የጉባኤው ተሳታፊዎች በንኡስ ጉባኤ እየከፈሉ ፤ በሰፊው ተወያይተውባቸው የጉባኤው ውጤት በውሳኔና በማሳሰቢያ መልክ በጉባኤው መጨረሻ ዕለት ለብፁዕ ወቅ ዱስ ፓትሪያርኩ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት ፤ ታላላቅ ካህናትና ምእመናን በተገኙ በት በቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን በታላቅ ሥነ ሥርዓት ቀርቦ በንባብ ከተ ሰማ በኋላ በቅዱስ ሲኖዶስ ዘንድ ተቀባይነት በማግኘት ጸድቋል ።

በዓለ ሢመቱንና ርክበ ካህናትን ምክንያት በማድረግ ለታቀደው ለዚህ ታላቅ ጉባኤ ብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ቤተ ክር ስቲያንና ምእመናን መተባበር እንዳለባቸው በማስረዳት የመምሪያ ንግግር በማድረግ ቃለ ቡራኬ ሰጥተዋል ። ከንግግራቸው በከፊል ለመጥቀስ ያህል ፤

“ : : : : : ዛሬ እዚህ የተሰበሰብነው በቤተ ክርስቲያን በኩል ያለብንን የጋራ ግዴታ ችንንና ኃላፊነታችንን ለመወጣት የምንችልበትን መንገድ ለመፈለግና ለማግኘት ነው ።

በአሁኑ ጊዜ ያለው የቤተ ክርስቲያናችን ኃላፊነት በመንፈሳዊ አገልግሎት ማለት ክህነት በመስጠት ፤ በማጥመቅ ፤ በማቁረብ ፤ በመባረክና ንስሐ በመቀበል ሥርዓት ተክ ሊልና ጸሎተ ፍትሐት በማድረስና ይህን የመሳሰለውን መንፈሳዊ አገልግሎት ለምእመ ናን በማበርከት ብቻ የተወሰነ አይደለም ፤ ማስተማርና የበጎ አድራጎት ሥራዎችን ማቋ ቋም በትምህርትና በሥነ ጥበብ ፤ በባህልና በታሪክ ረገድ ለረዥም ዘመን የአገራችን ባለ አደራ ሆና ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገረውን ይዛ ያቆየችውን ቅርስ መጠበቅና ሕዝቡ በልማት ሥራ ተካፋይ ሆኖ በኑሮው እንዲሻሻልና እንዲጠቀም ማበረታትና መር ዳት ይህ ሁሉ ሙያና አገልግሎት ቀድሞም የነበረ ቢሆንም በተስፋ በአሁኑ ዘመን ከመ ቼውም ጊዜ ይልቅ ከቤተ ክርስቲያን የሚፈለግ ግዴታና ተግባር ሆኖ ተገኝቷል ። ይላል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ነታቸው ያደረጉት የመምሪያ ንግግርና የሰጡት ቃለ ቡራኬ ሙሉ ቃል በገጽ ፳፰ ሲገኝ ፤ ጉባኤውም ተወያይቶ ያቀረባቸው ውሳኔዎ ችና ማሳሰቢያዎች በዚሁ መጽሔት ከገጽ ፴፫ እስከ ገጽ ፵ ሠፍረው ይገኛሉ ።

እንዲሁም በጉባኤው ላይ የንግግርና የማብራሪያ መግለጫ የሰጡት ሊቃውንት ሀሳብ በአስተዋጽኦመልክ ከገጽ ፶ እስከ ገጽ ፶፯ ባለው ላይ ተመልክ ቷል ።

ከዚህ ሌላ በጉባኤው ውይይት ጊዜ የተነሱ አንዳንድ ዋና ዋና ጉዳዮች ርእስ እየተ ሰጣቸው በዚሁ መጽሔት ውስጥ ተብራርተው ቀርበዋል ። እንዲሁም የዐቢይ ጉባኤ ውን (የበዓለ ሲመቱን ጉባኤ) ውይይት ማሳሰቢያና ውሳኔዎች መነሻ በማድረግ ከዚ ያን ወዲህ የተፈጸሙ የአንዳንድ ንዑሳን ጉባኤዎች ፍሬ ሀሳቦች በመጠኑ በዚሁ መጽ ሔት ውስጥ ተገልጸዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

የብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ

የሁለተኛው ዓመት የፓትሪያርክነት በዓለ ሢመት አከባበር ፤

# ሥነ ሥርዓት ፤

፩ኛ/ ብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሆነው የተሾሙበት የሁለተኛው ዓመት በዓለ ሢመት ግንቦት ፩ ቀን ፲፱፻፷፬ ዓ / ም በመላ የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ተከብሯል ።

፪ኛ/ በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ በመንበረ ፓትርያርክ አዳራሽ ከሚያዝያ ፳፰ ቀን ፲፱፻፷፬ ዓ/ም ጀምሮ ፯ ቀን ያህል ከዚህ ቀጥሎ በተጻፈው ሥነ ሥርዓት መሠረት ፤ በጉባኤና በልዩ ልዩ ዝግጅት ተፈጽሟል ።

፫ኛ/ ለዚህ በተዘጋጀው ሥነ ሥርዓት ላይ ፣

- ሀ/ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት ፤
- ለ/ የቤተ ክህነት ሹማምንትና ሊቃውንት ፤
- ሐ/ ከየሐገረ ስብከቱ ተወክለው የመጡ ካህናትና ምእመናን ፤
- መ/ የአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎችና የምእመናን ወኪሎች ፤
- ሠ/ ጥሪ የተደረገላቸው የመንግሥት ባለሥልጣኖች ና የልዩ ልዩ ድርጅቶች ተጠሪዎች ተካፋዮች ሆነዋል ።

፬/ ጉባኤ ፣

- ሀ/ ረቡዕ ሚያዝያ ፳፰ ቀን ፲፱፻፷፬ ዓ/ም ርክበ ካህናት ስለሆነ ፤ ከቀትር በኋላ በ፲ ሰዓት ብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ በተገኙበት በመንበረ ፓትሪያርኩ አዳራሽ ጉባኤው በሥነ ሥርዓት ተከፍቷል ።
- ለ/ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትሪያርክ ስለቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሥራና ርምጃ የመክፈቻ ንግግር አድርገዋል ።
- ሐ/ በዚሁ ሥነ ሥርዓት መደበኛው የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ተጀምሮ በተለይ በወጣው ሥነ ሥርዓት መሠረት ስብሰባው እስከ ሚያዝያ ፴ ቀን ፲፱፻፷፬ ዓ/ም ቀጥሏል ።
- መ/ ከምሽቱ በ፲፪ ሰዓት ከ፴ "ቤተ ክርስቲንና ምእመናን" በሚል ርእስ ንግግር ተደርጓል ።

www.ethiopianorthodox.org

# የጉባኤው ተሳታፊዎች ፤

፩/ ስለበዓሉ ታላቅነት የበዓሉን አንደኛ ዓመት ለማክበ ርብቻ ሳይሆን ፤ ይህን ታሪካዊ የሆነ በዓል ፩ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ በተዘጋጀው የሊቃውንት ጉባኤና የምዕመናን ጠቅላላ ውይይት ላይ ለመገኘት ከአዲስ አበባ ገዳማትና አድባራት እንዲሁም ከኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶች ታላላቅ የደብርና የገዳማት አለቆች አስተዳዳሪዎችና አበወምኔትጥሪ ተደርጎላቸው የመጡትና በበዓሉ ላይ የቆዩት ቀጥሎ የተመለከቱት ናቸው ።

## ፩/ ከአሩሲ ሀገረ ስብከት ፤

፩/ መምህር ኃይለ ሥላሴ ወልደ ሥላሴ የጠ/ግዛቱ ሊቀ ጳጳስ እንደራሴ ፤
፪/ አቶ ስምዐ ጽድቅ ኮንከ የሐገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ፤
፫/ መምሬ ሙሉጌታ ወ/ጻድቅ የካህናት አስተዳደር ፍ/ቤት ዳኛ ፤
፬/ መምህር ገ/ማርያም ወልደ ገሪማ የዝዋይ ገዳም አስተዳዳሪ ፤

## ፪/ ከትግሬ ሀገረ ስብከት ፤

፩/ መልአከ ምህረት ያሬድ ግርማይ የጨለቆት ሥላሴ አስተዳዳሪ ፤
፪/ ቀሲስ ሀብተ ማርያም ተድላ የሀገረ ስብከቱ ትም/ስብከት ኃላፊ ፤
፫/ መልአከ ብርሃናት ሐዋዝ ኃይሉ የአድዋ ሥላሴ አስተዳዳሪ ፤

## ፫/ ከወሎ ሀገረ ስብከት ፤

፩/ አለቃ መርዓዊ ወንድ አውል የደሴ መድኃኔ ዓለም ሰባኪ ፤
፪/ መርጌታ ስብሐት ገ/ጻድቅ የየጁ አውራጃ ግዛት ሰባኪ ፤
፫/ ቄስ ኢያሴው ቀጸላ የደሴ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ት/ቤት ሥራ መሪ ፤

## ፬/ ከወለጋ ሀገረ ስብከት ፤

፩/ አባ ወልደሐና ሀ/ ጊዮርጊስ የነቀምቴ ቅ/ማርያም ደብር አለቃ ፤
፪/ አባ ገ/ሥላሴ የሻነው የአርጆ ቅዱስ ገብርኤል ደብር አለቃ ፤
፫/ መምሬ ውሂብ ገብሩ የካህናት አስተዳደር ፍ/ቤት ዳኛ ፤
፬/ መምህር ዘወልደ ማርያም ቸሬ የደምቢዶሎ አውራጃ መምህር

## ፭/ ከጎጃም ሀገረ ስብከት ፤

፩/ መምህር ዳንኤል ባሳዝነው የደብረ ወርቅ ማርያም ገዳም አስተዳዳሪ ፤
፪/ መምህር ባሕርየ ድንግል ከዲማ ጊዮርጊስ ገዳም የመምህሩ ተወካይ ፤
፫/ አለቃ ወንድሙ እንዳለማው ከደብረ ማርቆስ ደብር ተወካይ ፤



www.ethiopianorthodox.org

፮/ ከሲዳሞ ሀገረ ስብከት ፤

፩/ መምህር ኃይለ ማርያም መሸሻ የወላሞ ደብረ መንክራት አቡነ ተክለሃይማኖት ገዳም አስተዳዳሪ ፤
፪/ አባሳሙኤል ኃይሌ በጀምጀም አውራጃ ግዛት የስብከተ ወንጌል ሠራተኛ
፫/ መምህር ገብረ ጻድቅ ወልደ አረጋይ የሲዳሞ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ግምጃ ቤትና ገንዘብ ያዥ ።

፯/ ከገሙጎፋ ሀገረ ስብከት ፤

፩/ መርጌታ ሐረገ ወይን ምሕረቱ የገሙ ጎፋ ሀገረ ስብከት ት/ቤቶች ሹም/
፪/ አባ ይትባረክ ተካልኝ የጨርጨር ማርያም ገዳም አስተዳዳሪ ፤
፫/ አባ ገብረ እግዚአብሔር አበራከሊቀ ጳጳሱ ላእካነ አርድዕት አንዱ ።

፰/ ከከፋ ሀገረ ስብከት ፤

፩/ መምህር ሀብተ ማርያም ደስታ የከፋ አውራጃ የስብከት መምህርና የቦንጋ ቅዱስ ሚካኤል አለቃ ፤
፪/ አባ እንግዳ ውበቱ የጅማ ደብረ መዊዕ መድኃኔዓለም ገበዝ ፤
፫/ አለቃ በየነ የኔነህ የአጋሮ ፈለገ ሰላም ቅድስት ማርያም አለቃ ።

፱/ ከኤርትራ ሀገረ ስብከት ፤

፩/ መምህር ተወልደ ብርሃን ወልደ ሥላሴ ከደብረ ቢዘን ፤
፪/ መምህር ቴዎድሮስ አፈወርቅ ከጸአዳ አምባ ሥላሴ ፤
፫/ መምህር የማነ ብርሃን ገ/መድኅን ከአቡነ እንድርያስ ስፍአ ፤
፬/ መምህር ተክለ ሃይማኖት ተስፋ ኃብር ከደብረ ሲና ፤
፭/ መምህር ኃይለ ማርያም ተስፋ ሥላሴ ከብፁዕ እምላክ ።

፲/ ከባሌ ሀገረ ስብከት ፤

፩/ መልአከ ሰላም ይትባረክ እምሩ የጎባ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ
፪/ መልአከ ገነት ወርቅነህ መንገሻ የጎባ ደብረ ገነት ቅድስት ማርያም አስተዳዳሪ
፫/ አባ ገብረ እግዚአብሔር ጸጋዬ የሀገረ ስብከቱ ምክትል ሊቀ ካህናት ፤

፲፩/ ከሐረርጌ ሀገረ ስብከት ፤

፩/ መምህር ተፈራ መልሴ የዐሰቦት ደብረ ወገግ ገዳም አስተዳዳሪ ፤
፪/ መምህር ኅሩይ መንግሥቱ የሐረር ደብረ ገነት መድኃኔ ዓለም ገዳም አስተዳዳሪ ፤
፫/ መምህር እሳቱ ወ/ማርያም የዓለም ማያ ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ፤

፲፪/ ከሸዋ ሀገረ ስብከት ፤

፩/ መልአከ ገነት ከፍ አለ በየነ የፍቼ ገነት ቅ/ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ ፤
፪/ አለቃ በዛ ረዴ የቁንዲ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ/ክርስቲያን አስተዳዳሪ ፤
፫/ ሊቀ መዘምራን ኃይለማርያም የረርና ከረዮ አውራጃ ሊቀ ካህናት

፲፫/ ከበጌምድር ሀገረ ስብከት ፤

፩/ መምህር በላይ መርሻ የጠ/ ግዛቱ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅና ሊቀ ካህናት
፪/ መልከ ተድላ ተስፋ ኢየሱስ ውቤ ፤
፫/ መልአከ ገነት አስካል በየነ

፲፬/ ከኢሉባቦር ሀገረ ስብከት ፤ በጊዜው ላይ ባለመድረስ አልተሳተፉም ፤

፲፭/ የአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት አለቆችና አስተዳዳሪዎች በዚሁ የጥናት ጉባኤና በዓል ላይ በመገኘት በሚገባ ተሳትፈዋል ።

## የ ን ግ ግ ሩ ተ ካ ፋ ዮ ች ፤

፩ኛ/ ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ፤
፪ኛ/ አቶ አክሊሉ አጥላባቸው ፤
፫ኛ/ የተከበሩ አቶ ሠይፈ ታደሰ ፤
፬ኛ/ አቶ አግደው ረዴ ፤
ሊቀ መንበር አቶ አበበ ከበደ ፤

፭/ ሐሙስ ሚያዝያ ፳፮ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም ፤

ሀ/ የጉባኤው ተካፋዮች "ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን" በሚል ርእስ በተደረገው ንግግር ከጥዋቱ ፬ ሰዓት እስከ ፮ ሰዓት ከቀትር በኋላ ከ፲ ሰዓት እስከ ፲፪ ሰዓት ድረስ ተወያይተዋል ።
ለ/ ከምሽቱ በ፲፪ ሰዓት ተኩል "ቤተ ክርስቲያንና ሥርዓቷ" በሚል ርእስ ንግግር ተደርጓል ።

### የንግግር ተካፋዮች ፤

፩ኛ/ አለቃ አያሌው ታምሩ ፤
፪ኛ/ ዶክተር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ፤
ሊቀ መንበር ዶክተር ታደሰ ታምራት ፤

፮/ ዓርብ ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም ፤

ሀ/ የጉባኤው ተካፋዮች "ቤተ ክርስቲያንና ሥርዓቷ" በሚል ርእስ በተደረገው ንግግር ከቀትር በኋላ ከ፱ ሰዓት እስከ ፲፪ ሰዓት ውይይት ተደርጓል ።
ለ/ ከምሽቱ በ፲፪ ሰዓት ተኩል"ቤተ ክርስቲያንና ርምጃዋ" በሚል ርእስ ንግግር ተደርጓል ።

### የንግግሩ ተካፋዮች ፤

፩ኛ/ ዶክተር ጌታቸው ኃይሌ ፤
፪ኛ/ አቶ ጌታነህ ቦጋለ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፫ኛ/ አቶ ሰሎሞን ጅሩ ፤
ሊቀ መንበር ክቡር አቶ አበራ ጀምበሬ ፤

## ፯/ ቅዳሜ ሚያዝያ ፳፰ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም ፣

ሀ/ የጉባኤው ተካፋዮች "ቤተ ክርስቲያንና ርምጃዋ" በሚል ርእስ በተደረገው ንግግር ከጥዋቱ ፫ ሰዓት እስከ ፯ ሰዓት ውይይት አድርገዋል ።

ለ/ ከጥዋቱ ፬ ሰዓት ጀምሮ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሰንበተ ክርስቲያን ት/ቤቶችና የወጣቶች አንድነት ማእከላዊ ጽ/ቤት ሥር በሚተዳደሩ የወጣቶችመንፈሳውያትማኅበሮች የሃይማኖተ አበው ፤ የተምሮ ማስተማር ፤ ሌሎችም ተመሳሳይ ማኅበሮች ያዘጋጁትና ተካፋዮች የሆኑበት ትርኢት በብፁዕ ወቅዱስ ፓትሪያርክ ቡራኬ ተከፍቶ ታይቷል ።

ሐ/ ከቀትር በኋላ በ፰ ሰዓት ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት በመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ዓምደ ሃይማኖት የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር የተዘጋጀው መንፈሳዊ ትያትር ታይቷል ።

## ፰/ እሑድ ሚያዝያ ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም ፣

ሀ/ ጥዋት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በአዲስ አበባ ገዳማትና አድባራት እያንዳንዳቸው በተመደበላቸው ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው ጸሎተ ቅዳሴና ስብከተ ወንጌል አድርገው ምእመናንን ባርከዋል ።

ለ/ የጉባኤው ተካፋዮች ጥዋት በጽርሐ ጽዮን ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን በማስቀደስ በአዲሱ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን የምረቃ ሥነ ሥርዓት ላይ ተገኝተዋል ። ከቀትር በኋላ አንዳንድ ድርጅቶችን ጐብኝተዋል ።

## ፱/ ሰኞ ሚያዝያ ፴ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓም ፤

ሀ/ ጥዋት ከ፫ ሰዓት እስከ ፯ ሰዓት የጉባኤው ተካፋዮች ማጠቃለያ ስብሰባ አድርገዋል ። በጉባኤው ላይ ልዩ ልዩ የተዘጋጁ መግለጫዎች ተሰጥተዋል ።

ለ/ በዚሁ ሰዓት የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ መደበኛ ስብሰባውን ፈጽሟል ።

ሐ/ ከቀትር በኋላ በ፱ ሰዓት ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ፤ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ፤ የጉባኤው ተካፋዮች ሁሉ በተገኙበት በተደረገው ጠቅላላ ስብሰባ የጉባኤው የመዝጊያ ሥነ ሥርዓት በጸሎት ተፈጽሟል ።

መ/ በዚህ ጊዜ ፣
፩ኛ/ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ፤
፪ኛ/ ከካህናት ፤
፫ኛ/ ከምእመናን ፤ መካከል ተቀዳሚ የሆኑ አንዳንድ ተጠሪዎች በተራ አጫጭር ንግግር አድርገዋል ።

ሠ/ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ቃለ በረከት ሰጥተው ጉባኤው በ፲፪ ሰዓት ተፈጽሟል ።



## ፲/ ማክሰኞ ግንቦት ፩ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም ፤

ሀ/ ለማክሰኞ አጥቢያ ከሌሊቱ ፰ ሰዓት ጀምሮ ከአዲስ አበባ አድባራትና ከየሀገረ ስብከቱ የመጡ ካህናት ለበዓሉ የሚስማማውን ስብሐተ ማኅሌት በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሲያደርሱ አድረዋል ።

ለ/ ጥዋት በ፲፪ ሰዓት ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ታጅበው ከቤተ ክርስቲያኑ ዓውደ ምሕረት ሲደርሱ ልብሰ ተክህኖ ፤ የለበሱ ቀሳውስትና ዲያቆናት ፤ የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ት/ቤት ተማሪዎች እየዘመሩ ተቀብለዋቸዋል ።

ሐ/ በበዓሉ ላይ እንዲገኙ ጥሪ የተደረገላቸው ክቡራን ሚኒስትሮችና ታላላቅ ሰዎች ከጥዋቱ ፲፪ ሰዓት ተኩል ጀምረው በየተመደበላቸው ሥፍራ ተገኝተዋል ።

መ/ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፤ልዑል አልጋ ወራሽና ንጉሣውያን ቤተ ሰብን አስከትለውና በክብር ተከታዮቻቸው ታጅበው ከጥዋቱ በ፩ ሰዓት ከቤተ ክርስቲያኑ እንደደረሱ ፤ ሥርዓተ ቅዳሴው በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ መሪነት ተጀምሮ ተከናውኗል ።

ሠ/ ሥርዓተ ቅዳሴው ከተፈጸመ በኋላ ፤ ለበዓሉ የታተሙ ሐዲስ ሕይወት
፩ኛ/ ትና ዜና ቤተ ክርስቲያን መጽሔችቶ ታድለዋል ።
፪ኛ/ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ጸሎተ ቡራኬ ሰጥተው ሠርሆተ ሕዝብ ሆኗል ።

፲፩/ በዚሁ ዕለት ከቀኑ በ፯ ሰዓት ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ለብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት ፤ ለክቡራን ሚኒስትሮች ጥሪ ለተደረገላቸው ታላላቅ እንግዶች ለየአድባራት አለቆችና መምህራን ለጉባኤው ተካፋይነት ከየሀገረ ስብከቱ ተወክለው ለመጡ ካህናትና ምእመናን በመንበረ ፓትሪያርኩ አዳራሽ ታላቅ የምሳ ግብዣ አድርገዋል።

፲፪/ ከዚህ በኋላ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል ።

www.ethiopianorthodox.org

የብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ የሁለተኛው ዓመት የፓትርያርክነት በዓለ ሢመት

# የአከባበር ሥነ ሥርዓት

ብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሆነው የተሾሙበት የሁለተኛው ዓመት በዓለ ሢመት ግንቦት ፩ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ ም በመላ የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ከፍ ባለ ሥነ ሥርዓት ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው ፕሮግራም መሠረት ተከብሮ ውሎአል ።

በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ በዓሉን ምክንያት በማድረግ በመንበረ ፓትርያርክ የስብከተ ወንጌል አዳራሽ ቀደም ብሎ ከሚያዝያ ፳፭ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ ም ጀምሮ ሰባት ቀን ያህል ፤

ሀ/ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት ፤
ለ/ የቤተ ክህነት ሹሞችና ሊቃውንት ፤
ሐ/ ከየሀገረ ስብከቱ ተወክለው የመጡ ካህናትና ምእመናን ፤



ከሚያዝያ ፳፭ —ሚያዝያ ፴/ ፷፩ ዓ፡ ም፡ በተደረገው ዐቢይ ጉባኤ በየዕለቱ ከተገኙት ካህናት ፤ ሊቃውንት ፤ መኳንንትና ምእመናን በከፊል ።

መ/ የአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎችና ምዕመናን ወኪሎች፤
ሠ/ ጥሪ የተደረገላቸው የመንግሥት ባለሥልጣኖችና የልዩ ልዩ ድርጅቶች ተጠሪዎች ተካፋዮች በሆኑበት ከፍተኛ ጉባኤ ሰፊ ውይይት ተደርጓል ።

የጉባኤውና የውይይቱም ውጤት በውሳኔ ጸድቆ ተላልፎዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

ከዚህ በኋላ ሰኞ ለማክሰኞ አጥቢያ ግንቦት ፭ ቀን ፲፱፻፰፬ ዓ ም ከሌሊቱ ፰ ሰዓት ጀምሮ ከአዲስ አበባ አድባራትና ከየሀገረ ስብከቱ የመጡ ካህናት ለበዓሉ የሚስማማውን ስብሐተ ማኅሌት በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሲያ ደርሱ አድረዋል ።

ከንጋቱ በ፲፪ ሰዓት ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ታጅበው ከቤተ ክርስቲያን ዓውደ ምሕረት እንደደረሱ ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ቀሳውስትና ዲያ ቆናት፤ የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ት/ቤት ደቀ መዛሙርት ፤

፩ኛ/ « ርቱዕ ይሠየም ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ቴዎፍሎስ ቅድመ
መጋቤ እግዚአብሔር ኃይለ ሥላሴ ፤
ዘዕሩይ ሢመቱ በሕገ ቀኖና ወርቱዕ ሃይማኖቱ ፤

ወሥነ አምልኮቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ፤
የሚለውን የግዕዝ መዝሙርና

እግዚአብሔር ጥበብ ነው የዕውቀት መጀመሪያ ፤
የሁሉ ፈጣሪ አምላክ ሃሌ ሉያ ፤

የእግዚአብሔር አምልኮት ከእኛ ጋር ከኖረ ፤
ነጻነት ይቆያል እንደተከበረ ፤

ኢትዮጵያ አገራችን ለምለሟ ተራራ ፤
ጠላት አይደፍራትም በተፈሪ ታፍራ ፤

በኃይለ ጸሎቱ ለቴዎፍሎስ ፤
አምላክ ይጠብቀን በሥጋ ወነፍስ ።

የሚለውን የአማርኛ መዝሙር እየዘመሩ ተቀበሉዋቸው ። ከዚያም በበዓሉ ላይ እንዲገኙ ጥሪ የተደረገላቸው ክቡራን ሚኒስትሮችና ታላላቅ ሰዎች ከጥዋቱ ፲፪ ሰዓት ተኩል ጀምረው በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ በተመደበላቸው ሥፍራ ተገኝተዋል ።

ቀጥሎም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልዑል አልጋ ወራሽ መር ዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴንና ንጉሣውያን ቤተ ሰብን አስከትለው በክብር ተከታዮቻቸው ታጅበው ከጥዋቱ በ፩ ሰዓት ከቤተ ክርስቲያኑ እንደደረሱ የጸሎተ ቅዳ ሴው ሥነ ሥርዓት በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ሠራዒነት (መሪነት) ተከናወነ ።

የጸሎተ ቅዳሴውም ሥነ ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ በኢትዮጵያ መንበረ ፓትርያርክ የስብከት የታሪክና የድርሰት ክፍል በተለይ ለበዓሉ ተዘጋጅተው የታተሙ ሐዲስ ሕይ ወትና ዜና ቤተ ክርስቲያን የተሰኙት መጽሔቶች በበዓሉ ላይ ለተገኙት ሁሉ ታድለው ፤ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ጸሎተ ቡራኬ አድርገው በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የሚደረ ገው ሥነ ሥርዓት እንዳበቃና ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በመጡበት አኳኋን ወደቤተ መንግሥታቸው ከተመለሱ በኋላ ፤ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ በቤተ ክርስቲያኑ ዓውደ ምሕረት ላይ ተገኝተው የበዓሉ ተሳታፊዎች ለሆኑት ምእመናን ሁሉ የፓትርያርክነት ማዕረግ ልብሳቸውን ተጐናጽፈው ፤ አክሊለ ክህነታቸውን ተቀዳጅተው አርዌ ብርት ይዘው በመታየት እንደቆሙ ፤ ከአዲስ አበባ አድባራት የተውጣጡ ጥንግ ድርብ የለበሱ ፳፬ መዘምራን ፤





ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ የመዐርግ ልብሳቸውን እንደለበሱ በቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ዐውደ ምሕረት ቆመው የካህናቱን ዝማሬ ሲያዳምጡ ።

በከመ ይቤሉ አዕማደ ሰላም ባስልዮስ ወቴዎፍሎስ ፤
አሠነየ ዓለመ እንተ በልየ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ፤
ማለት የሰላም ምሰሶዎች ባስልዮስና ቴዎፍሎስ እንዲከበሩ ንጉሠ ነገ ሥት ኃይለ ሥላሴ ያረጀውን ዓለም አደሰ (አሳመረ) የሚለውን ግሥ

ገሠው ፳ ደቂቃ ያህል አሸበሸቡ ።

በዚሁ ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም ጥቂቶቹ ወደ ቅዱስነታቸው በየተራ እየቀረቡ ስለበዓሉ ታላቅነት ንግግር አድርገዋል ። ልዩ ልዩ ቅኔዎችንና ግጥሞችንም አበርክተዋል ። ከቅኔዎቹም ጥቂቶቹን ከዚህ ቀጥለን አስገብተናቸዋል ።

<u>አንደኛ መወድስ ቅኔ ።</u>

ፍናወ መጻሕፍት ወለጠት መርዓተ ሕግነ ፤
ቤተ ክርስቲያን መርዓት ሕገ ብሉያት ቀዳማዊ ።
ወደኅራዊ ሥርዓተ ኖላዊተ ሐዲስ ኖላዊ ።
እስመ እንዘ ትሜህር ሕግጋተ ፤
እምላዕለ መርዓዊ ኀረየት መርዓዌ ።
መንግሥተ ስብሐት ቤተ መራዑ ፤
ዘበኃይለ ስብሐት ገፍትአት ዐራዌ ወሞዓባዌ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ለ ዓለ ም ።

መፍትውሂ ተሐድሶ ወሚጠተ ተድላ ምንታዌ ፤
ቤተ ክርስቲያን ምድረ ሳሌም ዘነበረት በጼዋዌ ።

ወድልው ትኅሥሥ ሆሣዕና ዳዊት ማሕየዌ ፤
ዳግመ ኢያልክፋ ኅምዘ አፍዖት ወኅምዘ አርዌ

## ሁለተኛ መወድስ ቅኔ ።

ንኡሰ ሰብእና ይትኤዘዝ ለበኵረ ሰብእና ፤
ወበኵረ ሰብእና ይትኤዘዝ ለሰብእናተ ዓፅም ንኡሳት ፤
ሥርዓታተ ዝኒ ንዘከር በእዝነ አእምሮ ሥርዓት ፤
ሩጸተ ከመ ይትኤዘዙ ሰባቱ ሀብታት ።
ለቃለ ዓዋዲ ቴዎፍሎስ
በተአግሦ ሀሊበ እለ ሐፀንዋ ትእዛዛት ።

## ለ ዓ ለ ም ።

በይምንሂ ወበጸጋም እመ ኢሀሎ መጽሔት ፤
እም ኢርእዩ ክሳውድ ፀዊረ ድማህ ምስለ ሥእርት ፤
ወከመ ኢኮኑ ላዕከ ለአፈ ልሳን አጽባእት ፤
አፈ ሰብእ እም ኢድኅነ ሐዊሮተ ታሕተ ኅሚሠፍት ። (ለኅሚሠፍት)
ፍት

ታደሰ ታየ ።

## አንደኛ ሥላሴ ቅኔ ።

፩ኛ/ ኖመ ድኅረ ሰክረ፤ኖኅ ዘሰትየ ወይነ ዚአሁ፤ወልብሰ ዚአሁ ፤
ገደፈ እንዘ የኃድግ ዕርቃነ፤ ዘሰትየ ባሕቱ ቴዎፍሎስ ወይነ ፤
ውስተ ቤተ መቅደስ ተአጽፈ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ብርሃነ ።
እስከ አሠረ ኖኅ ዘኢዴገነ ወበስቴ ወይን ንቁሐ ቴዎፍሎስ ኮነ ፤
እስከ አኮ ከመ ኖኅ አቡነ ።

## ፪ኛ ሥላሴ ቅኔ ።

፪ኛ/ ይጠበቡ በዓለሞሙ እምውሉደ ብርሃን ሰብአ ዓለም፤ ዘይቤ ወንጌል ፤
በቴዎፍሎስ ተአውቀ ፤
ቴዎፍሎስ አምጣነ በሥጋ ወበነፍስ ጸድቀ ።
እንዘ በሥጋሁ ይለብስ ኃመልማለ ወርቅ ረቂቀ ፤
ወበነፍስ ይለብስ ዘአንጸብረቀ ፤
ሐመልማለ ሰማይ ብርሃነ ዘይመስል ወርቀ ፤
እስመ ዝንቱ እምጌጋይ ርኅቀ ።



## ፫ኛ/ ሥላሴ ቅኔ ።

፫ኛ/ ሐሊበ ወመዓረ ዘታውኅዝ ምድረ ኢትዮጵያ፤ አወርሰከ ፍጹመ ይቤሎ
ኃይለ ሥላሴ ንጉሥ ፤
ለአብርሃም አበ ብዙኃን ቴዎፍሎስ ርእስ ፤
እስመ ከመ ለአብ አብርሃም ይቤሎ ወቃለ ዚአሁ ክርስቶስ ፤
ዕድዎ አንተ ለዮርዳኖስ ፤
ጥምቀተ ዮርዳኖስ ተውህበ ለቴዎፍሎስ ፤
እንተ ወርቅ መስቀሉ ቅዱስ ።

## መወድስ ቅኔ ።

፬ኛ/ ቴዎፍሎስ ወርቅ ጽሩየ ባሕርይ፤ኢይትዌለጥ ምንተ ከመ ኅብረ ፀምር ሎግዮ፤
ቅንአተ ጸላኢ እሳት እመ ፈድፋደ አውአዮ ፤
ለወርቅ ቴዎፍሎስ፤ እሳት ቅንዓተ ጸላኢ ዳዕሙ አርአዮ ።
እስመ ዘልፈ ንሬእዮ ፤
እንዝ ኢይትዌለጥ ምንተ ወኢይትገሰሥ ባሕርዮ ።

## ለ ዓ ለ ም ።

በይነ ወርቅሂ ቴዎፍሎስ እንዘ ገብር ሐልዮ፤
ላዕለ ወርቅ ቴዎፍሎስ ኢረከብነ አመክነዮ ፤
ቅንአተ ጸላኢ እሳት እንዘ ይጸድል ላህዮ ፤
ለወርቅ ቴዎፍሎስ አምጣነ ፈድፋደ አሠዮነ ።

አለቃ ተክለ ሃይማኖት እንግዳ ።

የሊቃውንቱ ንግግርና ቅኔ መስጠት እንደተፈጸመ በአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያናት ከመንፈሳውያት ማህበራት የተውጣጡ ደናግል ለቅዱስነታቸው ዕቅፍ አበባ አበርክተው በዓውደ ምሕረቱ የሚደረገው ጠቅላላ ሥነ ሥርዓት ተፈጸመ ። በዚሁ ዕለት ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያኩ ስለ በዓሉ ክብር ከቀኑ በ፲ ሰዓት ለብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት፤ለክቡራን ሚኒስትሮችና ጥሪ ለተደረገላቸው ታላላቅ ሰዎች፤ለአድባራት አለቆችና መምህራን፤ከበዓሉ አስቀድሞ በተደረገው ጉባኤ ለመገኘት ከየሀገረ ስብከቱ ተወክለው ለመጡ ካህናትና ምእመናን በመንበረ ፓትርያርኩ አዳራሽ ከፍ ያለ የምሣ ግብዣ አድርገዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

በግብገሯውም ላይ ሊቃውንት በየተራ ንግግር አድርገዋል ። ቅኔዎችንም አበርክተ ዋል ። የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ት/ቤት ደቀ መዛሙርትም እስከ ግብገሯው



ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩና ክቡር ጠ/ ሚኒስትር በግብገሯው ላይ ፤

ፍጻሜ ድረስ ልዩ ልዩ መንፈሳውያት መዝሙሮችን ሲያሰሙ ውለዋል ። ከዚያ በኋላ ጠቅ ላላ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል ።

በዓለ ሢመቱንና ርክበ ካህናትን ምክንያት በማድረግ ከሚያዝያ ፳፭/ ፳፬ ዓ/ም እስከ ሚያዝያ ፴/ ፳፬ ዓ/ ም ድረስ ለተደረገው የሊቃውንትና የምዕመናን ጉባኤ

# ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ የሰጡት መሪ ቃል

«የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ሰቦች
ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት
ካህናትና ምእመናን ፤»

«ይህ የዛሬው ቀን ጳጳሳት ፤ ካህናትንና ምእመናን ስለ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ተሰ ብስበን እንድንመካከርና እንድንነጋገር ከአባቶቻችን ከሐዋርያትና ከሊቃውንት ሲያያዝ የመጣ ለጉባኤ የተወሰነና የተፈቀደ ዕለት ነው ።

ጳጳሳት በየሀገረ ስብከታቸው ረዳቶቻቸው የሆኑትንካህናትንና ምእመናንን ይዘው ቢያንስ ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜያት እየተሰበሰቡ ግንኙነት እንዲያደርጉና ስለቤተ ክርስቲያን ጉዳይ እንዲወያዩ ፤ አስፈላጊውንም ሁሉ እንዲያሟሉ የቤተ ክርስቲያን የሕ ግና የሥርዓት መጻሕፍት ያዛሉ ፤ ከእነዚህም አንዱ በጥቅምት ፲፪ ቀን የሚደረገው ጉባኤ ሲሆን ፤ ሁለተኛው ደግሞ ከትንሣኤ በኋላ በአራተኛው ሱባኤ በሃያ አምስተኛው ቀን የሚውለው ርክበ ካህናት (መገናኛ)ተብሎ የሚጠራው ይህ የዛሬው ቀን ነው።



በዚህ ቀን አባቶቻችን እየተሰበሰቡ በመወያየትና በመነጋገር፤ በሃይማኖትና በመ ንፈሳዊ ሥራ ረገድ ለአገርና ለሕዝብ የሚጠቅም ብዙ ቁም ነገር ፈጽመውበታል ። ዛሬም እኛ ይህን ርክበ ካህናት የሚባለውን ዕለት ምክንያት በማድረግ የተሰበሰብነው የቆየውን በመከተልና በማስፋፋት እንጂ አዲስ ሥርዓት በመጀመር አይደለም ።



ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ጉባኤውን በቃለ በረከት ሲከፍቱ ።

አገራችን ኢትዮጵያ በነጻነቷ ተከብራ በታሪኳ ታውቃ በአቅዋሟ ጸንታ ለረጅም ዘመናት የኖረችው ያለ በቂ ምክንያት አይደለም።ከፈጣሪ የሚያገናኝና የሚያስተሳስር እውነተኛውን ሃይማኖትና በጎውን ምግባር ስለያዘች ነው ። ይህ መሠረታዊ አለኝታ ለሀገራችን እጅግ አስፈላጊ ነው ። ይልቁንም የሰው ልጅ በሥጋዊው ጥበብና በምድራ ዊው ሥልጣኔ እየተራመደ በሚሄድበት ጊዜ ይህ ለሕይወታችን አቋም መሠረትና ለችግራችን መድኅን የሆነው የሃይማኖትና የሥነ ምግባር ቅርሶችን በበለጠ መከባከብ ተጠብቆ ሊገኝ የሚገባው ነው ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለዚህ ብሔራዊ ለሆነው ለረጅም ጊዜ ተጠብቆ ለቆየው ቅርስ ባለቤትም ባለአደራም ሆና የኖረች ስትሆን በዚህ መጠን በአሁኑ ዘመንም ያለባት ኃላፊነት ከቀድሞው ቢከብድ እንጂ የሚቀንስ አይደለም ።

በእግዚአብሔር ቸርነት በግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ ትጋትና ዕድል ቤተ ክርስ ራሷን እንድትችልና በገዛ ልጆቿ እንድትመራ በመደረጉ ያለባት ኃላፊነትና ግዴታ ቲያን ከመቼውም ጊዜ ይልቅ የበለጠ አድርጓታል ። ይህንን ግዴታና ኃላፊነት የቤተ ክርስቲያን ዓባል የሆነ ሁሉ እንደየድርሻው የሚካፈለው ነው ።»

www.ethiopianorthodox.org

«ቤተ ክርስቲያን ብለን የምንጠራው ማንን ነው? ቤተ ክርስቲያን ስንል ምን ማለታ
ችን ነው? ካህኑም ምእመኑም ጳጳሳቱም ያሉበት ማኅበር አይደለምን? ቤተ ክርስቲያንን
የክርስቲያኖች ቤት የክርስቲያኖች አንድነት የሚያሰኛት? እንዲህ ከሆነ ጳጳሳት ብቻ
ሳይሆኑ ካህናትም ብቻ ሳይሆኑ ምእመናንም ጭምር በግልና በኅብረት የግዴታውና የኃ
ላፊነቱ ተካፋዮች ናቸው ማለት ነው ።



ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ለጉባኤው የመምሪያ ቃለ በረከት ከሰጡ በኋላ
ከአዳራሹ ሲወጡ ።

ዛሬ እዚህ የተሰበሰብነው በቤተ ክርስቲያን በኩል ያለብንን የጋራ ግዴታችንንና
ኃላፊነታችንን ለመወጣት የምንችልበትን መንገድ ለመፈለግና ለማግኘት ነው ።

በአሁኑ ጊዜ ያለው የቤተ ክርስቲያናችን ኃላፊነት በመንፈሳዊ አገልግሎት ማለት
ክህነት በመስጠት ፤ በማጥመቅ ፤ በማቁረብ ፤ በመባረክና ንሥሐ በመቀበል ፤ ሥርዓተ
ተክሊልና ጸሎተ ፍትሐት በማድረስና ይህን የመሳሰለውን መንፈሳዊ አገልግሎት ለም
እመናን በማበርከት ብቻ የተወሰነ አይደለም ። ማስተማርና የበጎ አድራጎት ሥራዎችን
ማቋቋም በትምህርትና በሥነ ጥበብ ፤ በባህልና በታሪክ ረገድ ለረዥም ዘመን የአገራ
ችን ባለአደራ ሆና ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገረውን ይዛ ያቆየችውን ቅርስ መጠ
በቅና ፤ ሕዝቡ በልማት ሥራ ተካፋይ ሆኖ በኑሮው እንዲሻሻልና እንዲጠቀም ማበረታታ
ትና መርዳት ይህ ሁሉ ሙያና አገልግሎት ቀድሞም የነበረ ቢሆን በተስፋ በአሁኑ ዘመን
ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ከቤተ ክርስቲያን የሚፈለግ ግዴታና ተግባር ሆኖ ተገኝቷል ።

ይህ ግዴታና ተግባር እንደ አስፈላጊነቱና እንደተገቢነቱ እየተሻሻለ በሥራ ላይ
ውሎ እንዲፈጸምና መልካም ፍሬ እንዲያፈራ የሁላችንን መተባበርና ተረዳድቶ መሥ
ራት ይጠይቃል ። ይህ መተባበርና ተረዳድቶ መሥራት እንዲኖር ለማድረግ ነው ዛሬ



ሁላችሁንም እዚህ የሰበሰብናችሁ።ከላይ የተገለጹትን የቤተ ክርስቲያን ተግባሮች በሥራ
ለመግለጽ የነበረውን የቤተ ክርስቲያን ሕግና መሠረታዊ አቋም በመከተል ሕዝበ ክርስ
ቲያን በሚኖርባቸውና ቤተ ክርስቲያን በሚገኝባቸው ሰበካዎች በየአጥቢያው የቤተ ክር
ስቲያን የሥራ ጉባኤዎችን በየደረጃው በማቋቋም ፤ የነበረውንም በማስፋፋት መሥራት
አስፈላጊ ሆኗል ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሀገረ ስብከት በተዘረጋበት ሥፍራ ሁሉ
በተሟላ ሁናቴ የሚቋቋመውና የሚደራጀው ይህ የየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ
በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ሰብሳቢነት ከካህናቱም ከምእመናኑም የተውጣጡ
ዓባሎች የሚገኙበት ሆኖ በዚያ ሰበካ ውስጥ ባለው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና ንብ



የአድባራት አለቆችና ካህናት የቅዱስነታቸውን የመምሪያ ቃለ በረከት በተመስጦ
ሲያዳምጡ ።

ረት አጠባበቅ የአገልግሎት አፈጻጸምና የትምህርት አሰጣጥ የስብከተ ወንጌል አመራርና
የበጎ አድራጎት አቀራረብ እንዲሁም ልማትንና ቤተ ክርስቲያንን በሚመለከት ማናቸ
ውም ጉዳይ በየሣምንቱና በየተወሰነ ጊዜ እየተሰበሰበ በምክር የሚሠራ ይሆናል ።»

«በየሀገረ ስብከቱ ውስጥ ያሉት እነዚህ የሰበካ ጉባኤዎች በዓመት ውስጥ በተወሰነ
ጊዜ በመንበረ ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ እየተሰበሰቡ በሀገረ
ስብከቱ ውስጥ ስላለው ቤተ ክርስቲያንን ስለሚመለከት ጉዳዩ እየመከሩ ይሠራሉ ።
በየሀገረ ስብከቱ ከካህናትና ከምእመናን መካከል የሚመረጡ ፤ ዓባሎች የሚገኙበት
የሀገረ ስብከት ጉባኤ በቋሚነት እንዲሠራ ይቋቋማል ።

ቤተ ክርስቲያን የጊዜውን ሁኔታ አስቀድማ በመመልከት የሚበጀውን ማደራጀ
ትና ሁሉንም በቀናው መንገድ ወደ በጎው ሕይወት መምራት ይኖርባታል ፤ ይህን ለማ
ድረግ ዘወትር ከጊዜው ቀድማ ማሰብ ማዘጋጀትና መሥራት ያስፈልጋል ። እንግዲህ
ችግራችን ምንድነው? መፍትሔውስ ምንድነው? ችግራችንና መፍትሔው ከታወቀስ

www.ethiopianorthodox.org

ባገኘነው መፍትሔ ችግራችንን የምናስወግደው እንደምን አድርገን ነው? ስለዚህ ነው ዛሬ ሁላችን እዚህ የተሰበሰብነው ።

በዚህ ረገድ ለተቀደሰው ዓላማ በአንድነት መገናኘትና ተባብሮ መሥራት የቤተ ክርስቲያናችንን ሕይወት የሚያድስ የአገራችንንም ዕድገት የሚያጎለምስ ስለሆነ ጌታ



የፓርላማ ዓባሎች ፤ ጥሪ የተደረገላቸው ታላላቅ ሰዎችና ካህናት የቅዱስነታቸውን ቃለ በረከት ሲያዳምጡ ፤

ችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ«ሁለት ወይም ሦስት ሆናችሁ በስሜ በተሰበሰባችሁበት እኔም ከዚያ በመካከላችሁ እገኛለሁ» ብሎ በሰጠን ቃል ኪዳን በመካከላችን ተገኝቶ ይህንን ጉባኤያችንን እንዲባርክልን እንለምነዋለን ። » በማለትመሪ ቃል ሰጥተዋል ።

# ጉባኤው ስለአስተዳደር ያደረገው ውሳኔ ፤

አስተዳደር ታላቅ ቃል ነው ። በውስጡም ብዙ አግጣጫ ያለው አስተሳሰብን ያቀፈ ጉዳይ ያለበት አፈጻጸም ነው ።

የብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስን ሁለተኛ ዓመት የፓትርያርክነት በዓለ ሢመት ምክንያት በማድረግ በተደረገው ዐቢይ ጉባኤ ላይ የተነሣው ጉዳይ ወይም ብዙ ሀሳብና አስተያየትም የተሰነዘረበት ይኸንኑ ርእስ «አስተዳደርን» የሚመለከት ነው ።

ያንድ ድርጅት መደርጀት ወይም መድከም ከአስተዳደሩ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል ። አስተዳደር በዕድሜ መብሰልን፤በእውቀት መደርጀትን፤ በአሠራር ልምምድ ዕድሜ መቁጠርን ይጠይቃል ። እምነትንና አደራ መባልን አገልግሎት መስጠት ማለትም ምን እንደሆነ ጠልቆ በመረዳት ሥራና ሠራተኛን የማገናኘት ዘዴን ወይም አገልጋይና ተገልጋይን ለይቶ በማወቅ አገልግሎት ሰጥቶ ወረታውን መጠየቅም ቀዳሚና ተከታይ መሆናቸውን አውቆ ኃላፊነትን በሚገባ ማስወረድ መሆኑን አዘውትሮ በማሰብ እያቀዱ መምሪያ አውጥቶ መሥራትና ማሠራት መሆኑን ያስገነዝባል ። ከዚህም ሌላ ፤

፩/ መመሪያ ደንብና ተቀባይነት ያለው ጊዜን የተከተለ ሥነ ሥርዓት እያወጡ ለሠራተኛው የማስረዳትን ፤ ሠራተኛው የሚሠራውን አውቆ እንጅ በመጠራጠርና በመሰለው እየሠራ ለራሱም በመመስገን ፈንታ ተወቃሽ ፤ ለባለአደራውም አስደሳች በመሆን ፈንታ አሳዛኝ እንዳይሆን መጠንቀቅን ፤ ተገልጋዩም ክፍል የሚሰጠውን ግልጋሎት አውቆ እንዲገኝ በማድረግ ለወሮታው እንዲዘጋጅ ማብቃትን ፤

፪/ የገቢ ምንጭ ማዳበሪያ ዘዴ እየፈለጉ በሚገኘው ሀብት ተገቢውን በጎ ሥራ በመሥራት አገልግሎት መሥጠት ፤

፫/ ለድርጅቱ መሠረታዊ አቋም ደህንነት በማሰብ ለአስተዳደሩና ለዓላማው ደጋፊዎችና የወደፊት ወገኖች የሚሆኑ ሰዎች (ምእመናን) ነባርነት ባላቸው ዓባሎች አማካይነት ለማፍራት ፤

ሀ/ የሕዝብ ግንኙነት ክፍል መመሥረት ፤

ለ/ ያለፈውን በማወቅ ያሁኑን በማየት የወደፊቱን በማሰብ ተገቢ ርምጃ ለመውሰድ ሁኔታን እያጠኑ የማንኛውንም የሥራ እቅድ ማውጣት ፤

ተገቢነቱን በማውሳት ይህን የመሳሰለውን ዘዴ ቤተ ክርስቲያን ምን ያህል ተጠቅማበታለች በማለት በመጠይቅ መልክ አስፈላጊነቱን የጉባኤው ውይይት አሳስቧል ።

፬/ ከዚህ አያይዞ ይበልጥ መግባባትና መቀራረብ ይኖር ዘንድ በጊዜው ቋንቋ መሥራት እንደሚያስፈልግና እንዳለፈው ሁሉ በዛሬው ጊዜም ትልቁን ነገር «ሃይማኖትን» ለወጣቱ ትውልድ በማስተላለፍ አማኝ አድርጎ የቤተ ክርስቲያን ልጅና አገልጋይ ለማድረግ መጣርና መሥዋዕት መሆን በመንፈሳዊና በሞራል ትምህርት ምእመናኑን ለመማረክ ከፍተኛ ተጋድሎ ማድረግ በሚያሻበት ባሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ፡

ሀ/ የተለመደውን መንፈሳዊ ትምህርቷንና የወንጌል ስብከቷን ከመስጠት እንዳትቦዝን ፤

ለ/ እንደቀድሞው ሁሉ ለምእመናን የሕገ እግዚአብሔርንና የሕገ ሰብእን ጠቃሚነት እያስተማረችና እያስረዳች ሕዝብ ከክርስቲያናዊ ኑሮና

www.ethiopianorthodox.org

አስተሳሰብ እንዳይወጣ የሚመክሩ ሐዋርያትን፤ ካህናትንና የወንጌል ሰባክያንን ከምእመ ናን ጋር ተባብራ በሚገባ እንድትይዛቸው ፤ ማስፈለጉ ተወስቷል ።

፳/ ከውስጥ ከስሕተት፤ከውጭ ከሐሜት ለመዳን የመግባቢያ ዘዴ መፍጠ ርና ግንኙነትን ከምእመናን ፡ ከድርጅቶችና ከሃይማኖት መሪዎችም ጋር በተሟላ ሁኔታ አበጅቶ ከሁሉ በፊት የድርጅቱን ክብርና ስም ከነ ታሪኩ በመጠበቅ ሥራውን በቅን ልቡና መሥራትና ማሠራት ፡ የተቀ ደሰ አገልግሎትን መስጠትና ተገቢ ወሮታውን ማግኘት አስተዳደሩ ይበልጥ ሊያስብበት የሚገባው መሆኑን የጉባኤው ተሳታፊዎች ከሆ ኑት ፺ (ዘጠና በመቶው) አበክረው አሳስበዋል ።

# “ አንፃር ፤ አስተያየትና አጻፋው ”

ቤተ ክርስቲያን ይህን ሠርታ ፈጸመች ፡ ወደፊት ይህን ታቅድና ትሥራ በተባለው መጠንም ባይሆን በዚሁ ዐቢይ ጉባኤና ከዚያም በኋላ በተደረጉት ተከታታይ ጉባኤዎች ላይ አልፎ አልፎ በወቀሳ መልክ የቀረቡ አልሠራችም፡አትሠራም፡ልትሠራምአትችልም



ብፁዐን ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት በሰባክያኑ ጉባኤ ላይ ተካፋዮች ነበሩ ።

አታስተምርም ወይም የሌላትን አላት በመባል ጭምር ከመወቀስ አልዳነችም ያላትንም ሀብት ሰብስባ መያዝ አልቻለች እንኳንስ በላዩ ልትጨምርበት ፤ ያላትንም ዓባሎች አልሰ በሰበች እንኳንስ አዲስ ዓባል ልትጨምር በሚል መንፈስ የተነጋገሩባት ዓባሎች አሉ። እነዚህን ዓባባሎች ሙሉ በሙሉ ሐሰት ለማለት ባይሞከርም በእውነትም ሆነ በይመ



ስላል ፡ ወይም በይሆናል ያለዚያም በጠላትነትና በምቀኝነት የሚወሩባትንም ቢሆን የሚነገሩባትን ተመሳሳይ ጉዳዮች ቤተ ክርስቲያን አልፎ አልፎም በትእግሥት ብታሳ ልፋቸውም ብዙዎችን እርግጥና እውነት ያልሆኑ መሠረትም የሌላቸው ሐሜቶች ወይም ወቀሳዎች መሆናቸውን በይፋ ገልጻ ከማስተባበል ወደኋላ አላለችም ።

ሀ/ አታለማም ወይም በልማት አትካፈልም ለሚባለው ጊዜና ዘመንን በተከተለ ሁኔታ ለመካፈል የወንጌል ልማት ኮሚሽንን አቋቁማ በብሔ ራዊ ደረጃ በመሳተፍ ላይ ናት ።

ለ/ አታስተምርም ለሚለው እስካሁን ትምህርትን ከእምነትና ከባህል ጋር አዋሕዳ ፤ በአንድነት የፍቅር ገመድ አስተሳስራ ለዘመኑ የትም ህርት አቋም ከማስረከቧም በላይ አሁንም ትምህርትብ ሔራዊና የሁሉም ድርሻ በመሆኑ እንኳንስ ሐዋርያዊት የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ራሷ ቀርታ ሌሎችም እንዲሳተፉበት እያሳሰበችና እየመከረች ፤ በጥን ቱና በአሁንም መልክ ትምህርትን እየሰጠች ናት ።

ሐ/ ሠራዊቷ ካህናት እንኳን ሊሠሩ የሚሠራውን ያወግዛሉ ለሚባለው እንኳንስ ሥራ በተባለው መስክና በፈጣሪ የተነገረውን «ብላዕ በሀፈ ገጽከ»የሚለውን መመሪያ ተከትሎ መሄድ ቀርቶና እንደ ካህን ለመቀደ ስና ለማጠን ብቻ እንዋ ልሳይሉ ሁለገብ በመሆን እንደወታደር ለመዝ መት ፡ እንደሐኪም ለመፈወስ ፡ እንደገበሬ ለማረስ ፡ በማንኛውም የል ማት ሥራ አባሪም አስተባባሪም በመሆን እንዲሠማሩ የካህናት ማሠ ልጠኛ ትምህርት (ኮርስ) የውይይት ጉባኤ (ሴሚናር) እያዘጋጀች ሠራዊቷን ካህናት ዘመናዊ ትጥቅ በማስታጠቅ ላይ ናት ።

መ/ ተከታይ አልጨመረችም ለሚባለው ሣይንስ ካስገኘው ውጤት ምኞት የተነሣ የሌላው ክፍል ተከታይ እየተራቆተ በሄደበት በአሁኑ ጊዜ የኢ ትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ግን ዓባሎች ያልተቀነሱ ፡ ሥርዓ ቶቿ ያልፈረሱ ፡ ዘመናዊና ወጣቱ ትውልድም በአቋሟ ባህላዊና ታሪ ካማ ፤ በእምነቷ ርትዕት እንደሆነች በመረዳት ፊቱን ወደርሷ መልሶ የወጣቶች ድርጅት እያቋቋመ በሰንበት ትምህርትና በበጎ ሥራ አገልግሎት እየገባ ክርስቲያናዊ ተግባር በማ ከናወን ወገኑን ሰብአዊ ፍጡርን ሲረዳና ቤተክርስቲያንን ሲያገለግል ይታያል ። ተጠሪዋም በመሆን ሥርዓቷንና ሕጓን በማስከበር፤እምነቷን በመጠበቅና በማስፋፋት ላይ ነው ።

ሠ/ እንኳንስ የሌላትን ፡ አላት የሚባለውን ጥቂት ሀብትና ንብረትም ቢሆን ከሠራዊቷ ካህናት ይልቅ ይበልጥ ተከታዮችዋ ምእመናን እንደሚገለገ ሉበትና እንደሚጠቀሙበት የታወቀ ነው ። ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ለራሷ ሳይሆን ስለክርስቶስ ለምእመናን ያለች ቅድስት የምእመናን ጉባኤ ናት ። በሷም ሁላችን ልንገኝባት ይገባናል ።

በክርስቶስ የተሰጠችንን ቤተ ክርስቲያን ልናማትም ሆነ ልንወቅሳት አይገባንም

www.ethiopianorthodox.org

# ቤተ ክርስቲያን ምንሠራች ? ወይስ እኛ ምን ሠራን ?

ቤተ ክርስቲያን ምን ሠራች ብሎ ከመጠየቅ ይልቅ ሕጓንና ሥነ ሥርዓቷን ጠብቀ
ንና ተከትለን እንዲሁም አክብረን ትምርቷንም ተምረንና አውቀን ሠራዊቷ የሆኑ ካህ
ናት ፤ እኛ ተከታዮችዋ የሆን ምእመናን ምን ሠራን ብለን ራሳችንን ብንጠይቅ ፤ የቤተ
ክርስቲያን አስተዳዳሪዎችስ ምን መምሪያ ሰጡ? በዚያስ አማካይነት ምን አከናወኑ?
ብንል በጋራ ኃላፊነት ላይ የተመሠረተ አድላዊ ያልሆነ አስተሳሰብ የያዘ መልስ እናገኛ
ለን ። አንዱ ሌላውን ወይም ሠሪ አሠሪውን ፣ አሠሪ ሠሪውን በመንቀፍ ብዙም ፋይዳ
አይገኝበት ውጤት የሚገኝ ፣ ሥራ የሚቃና ፣ሐሳብ የሚሠምር በመተባበር ነው ።

ለተጠየቀው ጥያቄ በቤተ ክርስቲያን በኩል መልሱ ቀላል ነው ። ከአፈጻጸሙ ላይ
ግን የብዙዎችን ተባባሪነት ይጠይቃል ።

በአዲሱ አስተዳደር የሥራ አመራርና እቅድ መሠረት ፤

፩/ ቤተ ክርስቲያን የዕውቀትንና የሰውን ኃይል በሚገባ በሥራ ላይ ለማዋል የካህ
ናትማሠልጠኛ ድርጅት አቋቁማለች ፤



ጉባኤው በንዑስ ደርግ እየተከፈለ በጉዳዩ ሲወያይ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፪/ በጠቅላላው የልማት ተግባር በብሔራዊ ደረጃ ለመሳተፍ የወንጌል ልማት
በማለት «የልማት ኮሚሽን» ጽ/ቤት መሥርታለች ፤

፫/ የክርስትና ትምህርትና የወንጌል ስብከት መስፋፋት ለምእመናን ኑሮ መድን
ይሆን ዘንድ በዘመናዊ መልክ የሰበካ ጉባኤ እያዘጋጀች ለወንጌል ሰባክያን
ተገቢ ትምህርትና የስብከት ዘዴ ማስጠናት ጀምራለች ፤

፬/ በሰንበት ትምህርትና በወጣቶች መንፈሳዊ ድርጅቶች መልክና አቋም የሥራ
እቅድና ድርሻ በመስጠት ወጣቱ የቤተ ክርስቲያን ልጅነቱን በማደስ ላይ
ነው ።

ይህን በመሳሰለው አማካይነት የተጨበጠ ነገር እየተካሄደ ነው ። ከዚህም የተነሣ
መቀራረብና መግባባት ተጠሪነትን ማወቅ የመሳሰሉት ሁሉ የትልሙ ውጤቶች ሁነ
ዋል ።

በቅርቡ ከታኅሣሥ ፳/፷፭ እስከ ጥር ፪/፷፭ ዓ ም ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ
ተማሪዎች ማኅበር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ርዳታና አማካይነት
ትልቁንና በዕድሜው ከ፹ ዓመት በላይየሆነውንየዓለም ክርስቲያን ተማሪዎች ፌዴሬሽን
(ኅብረት) በአፍሪካ ክፍለ ዓለም ሆነ በኢትዮጵያ ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ የተደረገውን
የድርጅቱን በየአራት ዓመት የሚካሄደውን ፳፯ኛ ጠቅላላ ጉባኤ በፌዴሬሺኑ ታሪክ
ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በሚገባ በማስተናገዱ ከፍ ሲል የኅብረት ሥራ ውጤቱ
ያማረ ነው ክብሩና ስሙም ለብዙ ነው እንደተባለው ምስጋናን ለአስተናጋጆቹ፡ ዝናን
ለሀገር፤ ታሪካማነትንና ተደናቂነትን ለቤተ ክርስቲያናችን አትርፏል ።

፭/ አኃቲ ቤተ ክርስቲያን በሚባለው መሠረት የቤተ ክርስቲያን ደንብና ሥርዓት
ወግን ሳይለቅ በሁሉም ዘንድ ተመሳሳይ እንዲሆን ቃለ ወንጌሉ ለምእመናኑ
እንዲሰማ ስብከቱ በአማርኛ ሥርዓተ ቅዳሴውና ጸሎቱ ከንጋት በኋላ እንዲ
ሆንና ምእመናን እንዲሳተፉበት በማድረግ ላይ ናት ። የአስተዳደሩም አቋም
ደንብን የተከተለ እንዲሆን ። በሰበካ ጉባኤ ክልል መሠረት መልክ እየያዘ ነው
፮/ ምእመናን በሚቻላቸው ጊዜም መጥተው እንዲጸልዩና በቤተ ክርስቲያን
አማካይነት ፈጣሪያቸውን እንዲማጸኑ በጠዋትና በሰርክ በተለይ በታላላቅ
ከተሞች የሚገኙ ቤተ ክርስቲያኖችና አድባራት ክፍት ሁነው ምእመ
ናን እንዲስተናገዱባቸው እያደረገች ናት ።
፯/ ከዚህም ሌላ የሕዝብ አገልጋዮች ካህናቷ የምእመናን ኑሮ አብነት የሚሆኑ
መምህራኗ የወንጌል ሰባክያኑና ሊቃውንቷ ታውቀውና ተከብረውም ተቀባይ
ነት እንዲያገኙ በደንብ ልብስ እያስለየች በትምህርተ መለኮት ጥልቅ እው
ቀት እየሰጠች በማሠማራት ላይ ናት ።
እነዚህም ሕገ እግዚአብሔርና ሕገ ሰብእን በማዛመድ በሚሰጡት ትምህርት የሕዝቡ
ኑሮና ችግር እየተቃለለ እንደሚሄድ ይታመናል። ሕገ ሰብእ በተለይም እንደኢትዮጵያ
ያለው ሕዝብ በእግዚአብሔር እምነት ያለው ሕጉ በዚያው በፈጣሪው ሕግና በሕዝቡ
ባህል ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ፤ ለሁለቱም ሕግ መገዛትን ማስተማርና ማሳወቅ ብልህ
ትውልድ ፤ ሠራተኛ ሕዝብ ፤ ታማኝ ዜጋ እርግጠኛ ምእመን ለማፍራት ያስችላል ።
እንዲህ ያለ ኅብረሰብእ ያለው አገርና መንግሥት በእውነቱ ከምንም ችግር ላይ አይ
ወድቅም ወይም ችግር አይገጥመውም ቢገጥመውና ቢወድቅም በፅንአቱ ፤ በአንድነቱ
በእምነቱ አሸንፎ ሊመለስ ቢወድቅ ሊነሣ ይችላል ።

# «ለቤተ ክርስቲያን ምን ያስፈልጋል ?»

የአስተዳደር ይዞታ የተቃና ፤ የትምህርት አሰጣጥ የሠመረ ፤ የስብከተ ወንጌሉ
«የሐዋርያዊው ድርጅት»ክፍል የተስፋፋ ሆኖ ተገቢውን የክርስትና ትምህርት ውጤት
ለማስገኘት የሊቃውንት ኃይል ፤ የተሟላ የመሣሪያና የድርጅት አቋም ማስፈለጉ የታ
መነ ጉዳይ ነው ።

ቤተ ክርስቲያን ቋሚና ተጠሪ ሰው በየግጣሜው ሊኖራት ስለማስፈለጉ እንደወ
ትሮው ሁሉ በጉባኤውም ሰሞን በተደረገው ውይይት ላይም ተደጋግሞ ተነሥቷል ።
፩/ ንብረት እንዳይባክን ፤ ሀብት እንዳይጠፋና እየለማ ከሥራ ላይ እንዲውል ከአ
ለው ለሌለው ከአገኘው ለአጣው እንዲሰጥ ንብረትና ሀብትን በሚገባ የሚቆጣጠር የን
ብረት አስተዳዳሪ (መጋቢ ሀብታት) ማስፈለጉን በመረዳት የ ር ሷ አዋቂ የራሷ
ሐኪም እንዲኖራት በማቀድ ከወጣቱ በስሟ ለማሠልጠን እንዲቻል ነጻ ትምህርት በማፈ
ላለግና በመሳሰለው ጉዳይ የልማት ኮሚሽን ይበልጥ እንዲረዳት ማስፈለጉን ፤ ራሱም
የልማት ኮሚሺን አቋምና ዓላማም ከቤተክርስቲያን ችግርና የሥራ አቋም ጋር ይበልጥ
የተባበረና የተዋሐደ እንዲሆን ጉባኤው አሳስቧል ።

፪/ ንብረት ጠባቂ እንደሚያስፈልግ ሁሉ ንብረት ን በሆነ ወይም ምክንያት በመ
ፍጠር ተጋፊና ዘራፊ ሲመጣ ሞግቶ በመርታት የሚያስመልስ ጠበቃና ፈጅ ማስፈለ
ጉን ፤ ይህ አቋም ባለመኖሩ ቢኖርም ካለ ባለመቆጠሩ ብዙ ንብረት የተወሰደባት መሆኑ
በጉባኤው ውይይት ጊዜ እንደማስረጃ ተነሥቷል።

ንብረትን መጠበቅ ብቻ ሳይሆን የማግኘትንም ዘዴ ጨምሮ የራስ ድርሻ የሆነውን
ማወቅ ተገቢ መሆኑ ተነሥቶ አገልጋዮች ሠራዊትን፥ተከታዮች ምእመናንንና ዱኩማንን
የሚረዳ ንብረትና ሀብት ማደራጀት ተወስቶ ለዚህም ሰው ማስፈለጉና ቤተ ክርስቲያን
እንኳንስ ከተከታዮችዋ የኔ ከሚሏትና ከምትላቸው ቀርቶ ተቃዋሚዎቿ ካልሆኑ ድርጅ
ቶች ሁሉ ለእምነቷ ማስፋፊያ ፤ ለሥነ ሥርዓቷ ማስከበሪያ ፤ ለአቋሟ መጠበቂያ ለትም
ህርቷና ለስብከቷ ማስፋፊያ ለትሩፋት ተግባሯ ማዳበሪያ የገቢ ምንጭ ማበጀት እንዳለ
ባት ጉባኤው በኃላ ድምፅ አሳስቦላት ፤ ሕዝቡን በሞራልና በግብረ ገብ አንጻ ለሕገ እግዚ
አብሔርናለሕገሰብእ እንዲገዛ የምትአስተምርና የምትመክር በመሆኗ እቅድዋንና ያሁ
ኑን ዓላማዋን በመደገፍ መንግሥት ተገቢውን የባጀትና የድርጅት ርዳታ እንዲያደርግ
ላት ጉባኤው ሲያሳስብ የርሷ ድርሻ ሊሆን የሚገባውን የገቢ ምንጭ በሕግ ጭምር
እንድታገኝ እንዲረዳት ፤ አስፈላጊነቱን አውስቶላታል ።

፫/ የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ባህልና ትምህርትም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃ
ውንት ሲጠበቅ የቆየና ለትውልድ የተላለፈ መሆኑ ታውቆ ተመዝግቦ ለወጣቱና ለመ
ጪው ትውልድ እንዲተላለፍ ቤተ ክርስቲያን ያሏትን ሊቃውንት ለዩንቨርሲቲ እያስ
ተዋወቀች በየሞያቸው ተሠይመው አስረጅ እንዲሆኑ ጉባኤው አመልክቷል ።

ለመንግሥት ጽንአት ፤ ለሕዝብ ደህንነት ፤ ለአገር ነጻነትና ሰላም ለኅብረሰብእ ብል
ጽግና የምትጸልይ አኃቲ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ድርጅቷ በዘመ
ናዊ እቅድና መልክ የተሟላ እንዲሆን ተገቢውንና ተፈላጊውን የሰው ኃይልና የተሟላ
የመሣሪያና የድርጅት አቋም በቅድሚያ ማግኘት እንዳለባት ጉባኤው ለዓባሎቹ ጭምር
በማስገንዘብ ይህ ዓይነት ችግር በአሁኑ ጊዜ መኖሩን ገልጾ ችግሩን ለመቋቋም የሚያስች
ለው የካህናትና የምእመናን መተባበር መሆኑን ጉባኤው አምኖበታል ።

www.ethiopianorthodox.org

ለሥራ በቅድሚያ ሠሪና መሣሪያ ያስፈልጋል ። ቀጥሎም ድርጊት የሚፈጸምበት
ነገር ወይም ውጤቱ የሚጠበቀው ጉዳይ ይፈጸማል ። ትምህርተ ክርስትናን ለምእመናን
በማስተላለፍ ለተደለደለ ሕይወተ ሥጋና ቡትስፋ ለሚጠበቀው ሰማያዊ ኑሮ ያለጥርጥር
ለማብቃት በቅድሚያ ትምህርተ መለኮትና ትምህርተ ክርስትናን ፤ ትምህርተ አበነ
ፍስና ሌላ ሌላውም ሁሉ ለካህናት በጥልቅና በርቀት መስጠት እንደሚኖርበት ፤ ለምእ
መናን እውነተኛውን እምነት ከነሥነሥርዓቱ አዘውትሮ ከኑሮ ጋር እያዛመዱ መስጠት ፤
ለአዲስ አማኝ በመጠኑ እያላመዱ ማስተማር እንደሚያሻ ዘዴውን አጥንቶ ለዚህም መመ
ሪያ ይሆን ዘንድ ለክህነት ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ፤ ለምእመናን እንደየደረጃቸው
የእምነትና የጸሎት መጻሕፍት በብሔራዊ ቋንቋ በቀላል አነጋገር የትምህርትና የስብከተ
ወንጌሉ መምሪያ ክፍሉ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግሥት ድርጅቶች ጋር በመተባ
በር እንዲያዘጋጅ የዐቢይ ጉባኤው የውይይት ደርግ በጥብቅ አሳስቧል ።

ስለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና አስተዳዳሪዎች መገልገያና መተዳደሪያ ሀብት
ተወስቶ ቤትና ንብረት ልጅ ወላጅ ላላቸው ካህናት የደመወዝ የሚያለሙትና የሚኖሩ
በት መሬት እንደየአቋማቸው እየታየ እንዲሠራላቸው በድንግልናና በምንኩስና ሥርዓት
ብቻ አምነው ለሚያገለግሉ ዓባሎች ለኑሮ የሚበቃቸው የተወሰነ የወር አበል ወይም በኅ
ብረት መተዳደሪያ የሚሆን ነገር ቢወሰንላቸው ለአስተዳደር እንደሚበጅ ተወስቷል ።

የቤተ ክርስቲያንና የምእመናን ግንኙነት በልደት ጊዜ ለጥምቀት ፤ በሞት ጊዜ ለፍ
ታት ብቻ ሳይሆን የዘወትር የቅርብ ግንኙነት እንዲኖራቸው ።

በአንድ ሰበካ (መንደር) ያሉት ካህናትና ምእመናን በመተዋወቅ ቢመዘገቡ ይጠቅ
ማል ።

በተለይ ካህናቱም ለቅስና አበነፍስ ለመሆን ለሰባኪነት ለሃይማኖትመምህርነት የሚያ
በቃቸውና የተመሰከረላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ መታወቂያ የልብስም ሆነ የወረቀት
መለያ ቢኖራቸው በየሞያቸው ከመታወቃቸውም ሌላ እንደየመዐርጋቸውም ለመከበር
ያስችላቸዋል ።

ከደብሩ አስተዳዳሪና ከሰበካ ጉባኤው ኃላፊ ሌላ ምእመናኑን በመመዝገብ አበወ
ነፍስ የሆኑትም ልጆቻቸውን ከነቤተሰባቸው መዝግበው ቢይዙ ለብዙ ጉዳይ ይጠቅማል።

የቤተ ክርስቲያንንና የምእመናንን መተባበርና መረዳዳት ከማረጋገጡ ሌላ ለሕያዋን
የሥርዓተ ጥምቀትንና የሥርዓተ ጋብቻንአገልግሎት ለመስጠት ፤ የሰንበት ትምህርትን
ለሕፃናትና ለወጣቶቹ ለማስተማር ፤ ለሙታን የሥርዓተ ፍትሐት ጸሎት ለማድረስ ከመ
ርዳቱ ጋር በማኅበራዊ ኑሮ በኩልም በዚህ አቋም አማካይነት ተጨማሪ ርዳታና ትሩፋት
ለማስጠናትና ለማቅረብ ማስቻሉ በውይይቱ ሳቢያ ተጠቅሷል ።

ካህናቱም ለዚህ የበቁ ሁነው መገኘት እንዳለባቸውና ቤተ ክርስቲያን የምትኮራባ
ቸው ምእመናን የሚያከብሯቸውና ቃላቸውን የሚቀበሏቸው መሆን እንደአለባቸው ተደ
ጋግሞ ተነሥቷል ።

ስለዚህ እንዲህ ያለውና የመሳሰለው አስተሳሰብ አሠራርና አያያዝ አስፈላጊነት
በጉባኤው ውይይት ጊዜ በብዙዎች ተደግፏል ። በሚቻልም በተግባር በቶሎ እንዲገ
ለጽ አሳስቧል ።

# የጉባኤው ፍሬያማ ውይይት

የጉባኤው ውይይት ውጤትና ፍሬ ሐሳብ በመሆን የቀረቡት ከ፲፭ ያላነሱ ዐበይት
ማሳሰቢያዎችና ውሳኔዎች ታላላቅ የሃይማኖት አባቶችና ሊቃውንት፣የመንግሥት ባለ
ሥልጣኖችና ምእመናን በተሰበሰቡበት በመንበረ ፓትርያርኩ ግቢ በምትገኘው ቅድስተ
ቅዱሳን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተለይ በተዘጋጀው ሥነ ሥርዓት ላይ
ብፁዕ ወቅዱስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ በተገኙ



ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በጉባኤው ፍጻሜ ብፁዐን ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት፤
የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና ታላላቅ ሰዎች በተገኙበት በመንበረ ፓትርያርክ
ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመደምደሚያ ቃለ በረከት ሲሰጡ ።

በት በንባብ ተሰምቶ ወዲያውኑ የቅዱስነታቸውን ቡራኬ በማግኘት ጭምር ማሳሰቢያዎ
ቹና ውሳኔዎቹ ወደፊት በሚቻል በኅብረት በሥራ ላይ እንደሚውሉና በተግባር እንደሚ
ገለጹ ቅዱስነታቸው የጉባኤውን ፍጻሜ ምክንያት በማድረግ ይህንኑ የጉባኤውን
ውጤት ለብፁዕ ወቅዱስነታቸው ሊያሰሙ ለቀረቡት አባሎችና ለሌሎቹም ተሳታፊዎች
በሰጡት የመልስ ቃለበረከት ላይ ሐሳቡን መቀበላቸውን አረጋግጠዋል ።

# ጉባኤው የተወያየባቸው አርእስቶች

በጉባኤው የቀረቡት ማሳሰቢያዎችና ውሳኔዎች ቀጥሎ የተዘረዘሩት ሲሆኑ እነሱም
በ፫ቱ ዋና ዋና የጉባኤ መወያያ አርእስት በነበሩት ፤

ሀ/ ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ፤
ለ/ ቤተ ክርስቲያንና ሥርዓቷ ፤
ሐ/ ቤተ ክርስቲያንና ርምጃዋ በተባሉት ላይ የተመሠረቱ ነበሩ ።

www.ethiopianorthodox.org

# የጉባዔ ውሳኔዎችና የማሳሰቢያዎች

# አ ስ ተ ዋ ጽ ዖ

የብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስን የሁለተኛ ዓመት የፓትርያርክነት በዓ ሢመት ምክንያት በማድረግ ከኢትዮጵያ አድባራትና ገዳማት ተመርጠው የመጡ ሊ ውንትና የደብር አለቆች፤አስተዳዳሪዎች እንዲሁም ከልዩ ልዩ ድርጅቶች ጥሪ የተደረገ ቸው ምእመናን በተገኙበት ከሚያዝያ ፳፰ እስከ ሚያዝያ ፴ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ ም ድረስ

ሀ/ ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ፤
ለ/ ቤተ ክርስቲያንና ሥርዓቷ ፤
ሐ/ ቤተ ክርስቲያንና ርምጃዋ በሚሉ አርእስት ላይ በቅድሚያ መግለጫ ማብራሪያዎች በምሁራን እየተሰጠባቸው ካህናትና ምእመናን እንዲሁም ሊቃውን ሁነው በጉባኤ መልክ ሲወያዩባቸው ቆይተው የሚከተሉትን ውሳኔዎች ለብፁዕ ወ ዱስ ፓትርያርክ ፤ ለቅዱስ ሲኖዶስ ለአስተዳደሩ ቦርድ ፣ ለቤተ ክህነት ዋና ሥ አስኪያጅ ተገቢው ርምጃ ተወስዶባቸው በሥራ ላይ እንዲውሉ በማሳሰብ ጉባኤ በትሕትና አቅርቧል ።

፩/ ጉባኤው ችግሯን አውቆ ቤተ ክርስቲያንን በበለጠ ለመርዳትና የምታደርገው ንም ጥረት ለመገንዘብ ስለቻለ ብፁዕ ወቅዱስንና አዘጋጆችን ከልብ እናመሰግኗል ፡

፪/ በዓለ ሢመቱን ምክንያት በማድረግ የተደረገው ታላቅ ጉባኤ ሊቃውንት ተገናኝተው ሐሳብ ለሐሳብ ለመለዋወጥ ምእመናኑም አስተያየት ለመስጠት በኅብረትም ችግሮችን አውቆ መፍትሔ ለመሻት የሚያስችል ሆኖ ስለተገኘ በየዓመቱ እንዲቀጥል ጉባኤው ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አሳስቧል ።

## ሀ/ ስለቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ፤

፩/ ቤተ ክርስቲያን ከምእመናን ጋር የምትገናኝበትን መንገድ በራሷ በመንግሥትና በግል ድርጅቶች አማካይነት ማጠንከር አለባት ።

የሰበካ ጉባኤ ሐሳብ ተደግፎ ሥራውን እንዲደረጅ ጉባኤው በጥብቅ አሳስቧል

፪/ ምእመናን ከቤተ ክርስቲያን እንዳይርቁ ካህናት የማስተማር ዘዴያቸውንና አ ልግሎታቸውን ከምእመናኑ አስተሳሰብና ፍላጎት ጋር የተዛመደ ያድርጉት ። ለዚህም ሥነ ሥርዓት የተከተለ መምሪያ ይዘጋጅላቸው ።

፫/ ቤተ ክርስቲያን ስንል ካህናትንና ምእመናንንያጠቃለለ ስለሆነ፤ቤተ ክርስቲ ያን የምእመናንን ኃላፊነት በሚገባ በማስረዳት የበለጠ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ታድርግ ።

፬/ ባሁኑ ጊዜ ወጣቶች ቤተ ክርስቲያንን በብዙ መንገድ ሊረዱ ስለሚሹ የአገ ልግሎት ድርሻቸው በትምህርት መልክ ተሰጥቷቸው የቤተ ክርስቲያን ልጆችና አገልጋ ዮች እንዲሆኑ ከቀድሞው በይበልጥ ማበረታታት ይገባል ።

ምእመናን ፤ ቤተ ክርስቲያንን የሚጠጓት በጥምቀት ፤ በጋብቻ ሥነ ሥርዓት ፤ በሞት ጊዜ ፤ በፍትሐት ብቻ ሳይሆን ፤ እንደቤታቸውና እንደንብረታቸው በማየት አዘው ትረው ስለእርሷ በማሰብ ተገቢውን ሁሉ በማድረግ እንዲጠብቋት የደብር አለቆችና አስ ተዳዳሪዎችም በየበኩላቸው እንዲያተጉዋቸው ማድረግ ይገባል ብሏል ።

www.ethiopianorthodox.org

ለ/ ስለቤተ ክርስቲያንና ስለሥርዓቷ ፤

፩/ ስለቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ለይቶ የሚገልጽ በቅዱስ ሲኖዶስ የጸደቀ በመምሪያ መልክ ተዘጋጅቶ ካህናቱም ሆኑ ምእመናኑ ጠንቅቀው እንዲያውቁ ይደረግ ።

፪/ የክርስቶስን ሥጋና ደም ለመቀበል ከኃጢአት ለመንጻት ፤ ብቁ ነን ብለው የሚቀርቡትን ሁሉ ፤ ቤተ ክርስቲያን እንድታበረታታቸው ማድረግ ተገቢ ነው ። ለነዚህ ምእመንና ስለቅዱስ ቁርባን አስፈላጊነት ትምህርት ይሰጥ ።

፫/ ሥልጣነ ክህነት ለሚቀበሉ ሁሉ ለዚያ ስለሚያበቃቸው ጠባይና ትምህርታቸው በቤተ ክርስቲያን የክህነት ትምህርት ደረጃ ሊኖራቸው ይገባል ።

፬/ ሥርዓተ ቅዳሴው ፤ እንደተለመደው በግዕዝ ማዜምም ስብከተ ወንጌሉና ንባቡ በአማርኛ እንዲሆንና ምእመናኑ እንዲረዱት ይደረግ ።

፭/ አሐቲ ቤተ ክርስቲያን ተብላ በአንድ ፓትርያርክ መሪነት የምትተዳደር ቤተ ክርስቲያን አንድ ዓይነት ሥነ ሥርዓትና ወግ ያላት መሆኑን ለማሳወቅ ፤ የቅዳሴው ሰዓት ፤ የምእመናኑ አቀባበልና የአግልግሎት መስጠት ጉዳይ እንዲስተካከል ፤ በሁሉም ዘንድ በሥራ ላይ የሚውል መምሪያ ይሰጥ ።

ሐ/ ስለቤተ ክርስቲያንና ርምጃዋ ፤

፩/ ቤተ ክርስቲያን በአለፈው በትምህርት ኮትኩታ በባህል አሠልጥና ምእመናንና ሊቃውንትን ለአገርና ለታሪክ ማበርከቷ በሰፊው የሚወሳ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ለመሻሻል የምታደርገው ጥረትና ተጋድሎ ተከታዮቿን ሊያበረታታ ይገባል ።

የቤተ ክርስቲያን የወደፊት ርምጃ የተቃና እንዲሆን በማመን ፤ የሌሎችንም እምነቶች ሰርጎ ግብነት ለመቋቋም ባዕድ አምልኮ ተከታዮችንም ለመመለስ በአስተዳደር ፤ በትምህርት በስብከተ ወንጌል ሙያና በሌላውም ተገቢ መሻሻልና ርምጃ ታድርግ ።

፪/ ጊዜ እየተለዋወጠ በመሄዱ ካህናት ለዚሁ ለውጥ የተዘጋጁ እንዲሆኑ በማሠልጠኛ መልክ ትምህርት በየሙያቸው እንዲሰጣቸውና አዲሶች አማንያንም ሆኑ ነባሮች ምእመናን በቂ የክርስትና ትምህርት እንዲያገኙ ይደረግ ።

፫/ የሃይማኖት ትምህርት በትምህርት ቤቶች በማሠልጠኛ ቦታዎችና እንዲሁም ባገልግሎት ሥፍራዎች እንዲሰጥ ይሁን ።

፬/ አዲስ የተቋቋመው የቤተ ክርስቲያን የልማት ኮሚሽን በመሠረቱ ቤተ ክርስቲያንን ለልማት ተሳታፊ የሚያደርግ መሆኑን ጉባኤው ሲስማማ ዝርዝር ጥናቱ የቤተ ክርስቲያንን ቅድሚያ ችግር ባለመገንዘቡ እንደገና እንዲመረመር ጉባኤው በትሕትና አሳስቧል ።

# ልማትና በልማት ተካፋይነት

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አዲስ ርምጃና የአሠራር ዘይቤ ፤ የተግባሯም ማስተባበሪያ አርማ አድርጋ የያዘችው የልማት ወንጌል (የልማት ኮሚሽን) የሚል የእቅድና የሥራ መመሪያ አቋም ነው ።

በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የወሰደችው ርምጃ የዓለም አስተዳደር ፤ የምእመናን ኑሮና ዓላማ ወይም አቋም ከጊዜ ወደጊዜ እየተለወጠ መሄዱን በመገንዘብ መሠረተ ትምህርቱን «ወንጌልን» ሳትለቅ የተለመችው ፈር ስለሆነ ልትመሰገን ይገባል ።

ቤተ ክርስቲያን ዱሮ ቅድሚያም የምትሰጠው ጥምቀት ፣ ክርስትና ከአረመኔነት ወደ ክርስትና መመለስን ብቻ ነበር ። አሁንም ይህ ሳይቀር ሆኖም ዛሬ ሥልጣኔ የሰውን ልጅ ስለገራው የክርስትና ሃይማኖትም ተስፋፍቶና ተራብቶ የብዙዎች ስለሆነ ድካሙና ችግሩ የዚያን ጊዜ ያህል አይደለም ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን አዲስ የአሠራርና የማስተማር ዘዴና ፈሊጥ የተስፋው ዓለም ሰማያዊውና የእንግድነት መኖሪያው ምድራዊው ዓለምም አስቸጋሪና አስከፊ እንዳይሆን ምእመናን ኑሮን አሟልተው በሕይወተ



ክቡር ንቡረ ዕድ ኤርምያስ ከበደ የጠ/ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ስለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቱያን የልማት ኮሚሽን ዕቅድና ርምጃ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ገለጣ ሲያደርጉ ።

ሥጋ የደረጁ ለሕይወተ ነፍስ የተዘጋጁ እንዲሆኑ በማስተማርና በማበረታታት እንዲሁም በማሳየትም ተካፋይ ለመሆን ተዘጋጅታ እስባበት ተነሥታለች ። ለዚህ ምስክሩ የልማት ኮሚሽን ማቋቋሟያና ፕሮግራም አውጥታ ከሥራ ላይ ማዋሏ ፤ ተካፋይ ለመሆን በተነሣችበትም አቅጣጫና የተግባር መስክ ላይ ይህም እንደትምህርት ፣ ጤና ፣ ጠቅላላ የገጠር ልማትና ርሻ በመሳሰሉት ፣ ሠራዊቷን አሠልጥና በሚገባ ለማሳተፍ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግሥት ድርጅቶች ጋር ከግንቦት ፲፯ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ ም እስከ ግንቦት ፲፰ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ ም ለሁለት ሙሉ ቀን የተደረገው ጉባኤ ትልቅ መረጃ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

በጉባኤው የመግቢያ ንግግር ላይ በዋናው ሥራ አስኪያጅ በክቡር ንቡረ ዕድ ኤር ምያስ ከበደ የተደረገው ገለጻ ፍሬ ሐሳቧንና የነበረና ያሁን እንዲሁም የወደፊት አቅ ዷን ይገልጸል ። በጥቂቱ ለመጥቀስ ያህል ።

«ቤተ ክርስቲያን በሃይማኖትና በመንፈሳዊ ሕይወት ብቻ ሳይሆን በትምህርት ፤ በኪነ ጥበብ ፤ በአስተዳደርና በዳኝነት ፤ በማኅበራዊ ኑሮና በፀጥታ ጥበቃ ፤ በግብርናና በልማት ሥራ ሁሉ ለአገር ያበረከተችው አገልግሎት በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። ይህ ለረጅም ዘመናት ሲያያዝ የመጣ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ዛሬም ወደፊትም ሊቀጥል የሚገባው አስፈላጊነቱና ፍቱንነቱ የተረጋገጠ ዓይነተኛ ጉዳይ ነው ።»

«ቤተ ክርስቲያን ይህንን ሲያያዝ የመጣ በብሔራዊ ደረጃ የተዘረጋ ሙያዋንና አገ ልግሎቷን ዛሬ ዘመኑ በሚጠይቀውና የንጉሠ ነገሥት መንግሥት ካዘጋጀው እቅድ ጋር በሚስማማ መልክ አደራጅታና አስፋፍታ መቀጠል ያለባት መሆኗን በመረዳት በተለይ ለዚህ ዓላማዋ አፈጻጸም እንዲረዳ በቅርቡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የል ማት ኮሚሽን በሚል ስያሜ አንድ ድርጅት አቋቁማለች ።

«ቤተ ክርስቲያን ያላትን የእውቀት ፤ የሀብትና የሰው ኃይል እንዴት በምንስ ሁኔታ በሥራ ላይ አውላ ራስዋን፤ ቤተሰቦችዋን፤ ካህናትንና ምእመናንን በጠቅላላውም አገሪ ቱን ለመጥቀም እንደምትችል አጥንቶ የሥራ ውጤት ማግኘት የዚሁ ድርጅት ዓይነተኛ ዓላማ ነው ።» በማለት አስረድተዋል ።

በጉባኤው የተሳተፉት የመንግሥት ድርጅቶች ፤ ባለሥልጣኖች የዩንቨርሲቲ ምሁ ራን የሆኑ ሊቃውንት ቤተ ክርስቲያን ሰፊ የልማት ድርሻ እንዳላትና ሥራውንም ለመ ሥራት ወይም በሥራው ተሳታፊና ተባባሪ ለመሆን እሙን የሆነ የሰው ጉልበት የእውቀ ትና የመሣሪያም ሀብት ያላትና ተደማጭ በሆነው ቃሏ ሥራውም እንደሚቀናላት ውጤ ቷም እንደሚያምር ተሳታፊዎቹ በያደረጉት ገለጻ ድምፃቸውን በማስተባበር መስክረ ዋል ። በአጠቃላይ በአለፈው ጊዜ በንቃትና በትጋት መንፈስ ያቆየችው የእድገት ፍልስ ፍናን ባህልንና ፍትሕን የመጠበቅ ተግባሯን አሁንም ሊቀጥል እንደሚገባው ጉባኤው በውሳኔ መልክ አሳስቧል ።

ስለዚህ ችሎታ እንዳላት የተመሰከረላት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በሠራዊቷ ካህናት አማካይነት ድንቁርናና ድህነት ጠፍቶ የተስተካከለ ፍርድና ኑሮ በሚገባ ተመሥርቶ ፤ ሥጋዊ ኑሮ ተቃንቶ ፡ አገርና ሕዝብ ለሰላማዊ ኑሮ በቅቶ ሕዝቡ ከኑሮ ችግሩና ከሐሳብ ጭንቀት ተለይቶ በመጨረሻም ዘለዓለማዊ የሆነውን በተስፋ የሚ ጠበቀውን ሰማያዊ ኑሮና ሕይወት ያገኝ ዘንድ ተከታዮችዋ ምእመናንን በሚገባ ልት መራና ለዚህም ልታበቃ ስለሚገባ ኃላፊነቷና ባለአደራነቷ ትልቅ ነው ። በውይይቱም ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፍርድ አስፈጻሚ ፤ መብት አስከባሪ ሆና በማገልገል እንደእናት በመቅጣትና በመምከር ፤ አንድ ዓይነት ነገር ሲመጣ ይበጃል አይበጅም ብሎ በማስረዳት ፤ ከክፋት ወደ ደግነት ፡ ከስንፈት ወደ ትጋት ፤ ከመለያየት ወደ አንድነት የሕዝቡን መንፈስ በማምራት ፡ ከቤተመንግሥቱ ጋር እንደሥጋና ነፍስ ሆና የቆየች መሆኗ ተወስቶ አሁንም ይህን በሰፊው በዘመናዊ መልክ ለመፈጸም ጠቅላላ በብሔ ራዊ ልማት ለመካፈል ያደረገችው ቁርጥ ሐሳብ ተደንቋል። መእመናኑ በተለይም ወጣቶ ችም የሐሳቧ ደጋፊዎች ፤ የምኞቷ ፈጻሚዎች በመሆን ከልብ በልዩ ልዩ ፕሮግራሟ እንደሚሳተፉም ተስፋ ተደርጓል ።



ቤተ ክርስቲያናችን የዘመንን ጎዳና ተጉዛ ፤ የጊዜን ማእበል ተቋቁማ እስካሁን ጠብቃ በማስተላለፍ ያቆየችልንን ጸጋ ያለው ባህልና ርቱእነት ያለው እምነት ከነት ምህርቱ ጠንክሮና ዘመናዊነትን ይዞ ለዘመኑ ትውልድ በማስተላለፍ ትውልዱን እው ነተኛ ኢትዮጵያዊ ለማድረግ ይበልጥ በመሥራት እንድትካፈል ስለልማቱ የተሰበሰበው ጉባኤ አበክሮ አሳስቧል ።

# የዐቢይ ጉባኤው ተከታታይ ጉባኤዎች

ሀ/ የበዓለ ሢመቱ ጉባኤ እንዳለቀ ቀጥሎ የተደረገው ፪ኛው ጉባኤ ከግን ቦት ፲፮—፲፯ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ/ም በቀ ፡ ኃ ፡ ሥ ፡ ሽልማት ድርጅት አዳራሽ ውስጥ ከመን ግሥት ድርጅቶች የትምህርትና የልማት ክፍል ኃላፊዎችና ታላላቅ ባለሥልጣኖች የዩኒቨርሲቲ ሊቃውንትና ጥሪ የተደረገላቸው የዓለም አብያተ ክርስቲያን አማካሪም ከጄ ኔቭ የተገኙበት የወንጌል ልማት ወይም የልማት ኮሚሽን ያዘጋጀው ጉባኤ ነው ።

በዚህ ጉባኤ የልማት ኮሚሽን ቤተ ክርስቲያን በአቋም ደርጅታ በምግባረ ሠናይ እቅድዋና በልማት ተካፋይነት ፕሮግራሟ በጠቅላላው ስብከተ ወንጌልን ስታካሂድ በዘመናዊ ርምጃዋ የተሳካ ውጤት እንድታስገኝ ፤ ለመርዳት ከሌላም የልማት ድር ጅት ጋር ለመሥራት እንድትችል ፕላኗን የሚያቀርብላትና የሚያስተባብርላት በመሆኑ የኮሚሽኑ ዓላማና አቋም በዚሁ ጊዜ ከመገለጹ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ምን ስትሠራ ፤ ስት ፈጽምና ስታስፈጽም እንደነበረች ሁሉ ተወስቶ አሁንም ቀድሞ ትፈጽመው የነበረውን እንደ ትምህርት መስጠቱን ፤ በሞራልና በግብረ ገብ ሕዝቡን ማነጽን፤በመንፈሳዊ ምክር ምኞቱን ማርካቱን ፤ ስለእውነት መመስከርን፤ ፍትሕን መጠበቅ ፤ ለወጣቱም ሆነ ለአ በው እውነት ነፃ የምታወጣ መሆኗን እንደ ጥንቱ በማስተማር በእውነት መክሮና አስ ተምሮ ከክፉ ወደደግ፤ ከብቸኛነት ወደ ማኅበራራዊነት መመለስ፡ከግል ይልቅ ለሕብረት ማሰብን ፤ ከኃሳ ይልቅ ለብሔራዊ አቋም መቆርቆርንና እኒህን የመሳሰሉትን መልካም ዜጋና እውነተኛ ክርስቲያን ሊከተላቸው የሚገባቸውን ተግባሮች አሁንም ታስፈጽም ።

አሁን "ልማት" ተባለ እንጂ ጌታችን መድኃኒታችን"ላገለግል መጣሁ"ባለው መሠ ረት አገልግሎት በተባለ ጥሩ ነበር።ሆኖምየቤተ ክርስቲያንሠራዊት ካህናት ከመንግሥት የልማት ድርጅት ሰዎች ጋር ሁነው እያስተማሩና እየመከሩ እየሠሩ ምበማሳየት ጭምር ተሳታፊዎችና አባሪዎች እየሆኑ ሕዝቡን ከችግር ማጥ ሊያወጡት ይገባል ። እስካሁን በአፍ ብቻ ይነገር የነበረውን ከእንግዲህ በግብር ለመግለጽ ካህናትን በየሙያው መስ መር በማሰልጠን ሁለገብ ሁነው በማገልገል እንዲሠሩም ሆነ ሕዝቡን እንዲመክሩ ቤተ ክርስቲያን በማሰቧ ያስመሰግናታል። ሐሳቧም ውጤት እንዲኖረው እንተባበራለን።

ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ የማኅበራዊ አገልግሎት ሰጪና መሥራች እንደ ነበረች ሁሉ አሁንም ለማኅበራዊ ድርጅት ዓምድና አርማ በመሆን ማገልገል ትችላለ ችና በሐሳቡ ትግፋበት፤ በማለት ጉባኤው በአንድ ድምፅ ድጋፍ በመስጠት ጭምር ተስ ማምቶ ቤተ ክርስቲያንም በምን በምን ለመሳተፍ እንደምትችል ወይም ልካፈል ብላ በመጠየቅ በተነሣችበት አቅጣጫ ምን መከተል ወይም በምን መደራጀት እንዳለባትና በትምህርት መልክ ለሠራዊቷ ካህናትም ስለምትሰጠው የሙያ ኮርስ የትምህርት ሥነ ሥርዓቱ ከምን የሙያ ምንጭ የተውጣጣ ሊሆን እንደሚገባውና የቱን በቅድሚያ ማድ

www.ethiopianorthodox.org

ረግ እንዳለበት በማስገንዘብ ምክሩን ለግስዋል ። ለዚህም አስፈላጊ የሚሆኑትን የመሣሪያም ሆነ የሰው ኃይል ርዳታ ከየትና ከነማን ድርጅቶች እንደምታገኝ አመልክቷል ።

ለ/ ሁለተኛውና ተከታይ የሆነው ሌላ ዐቢይ ጉባኤ ደግሞ በ፲፱፻፷፩ ዓ ም ከነሐሴ ፳፱—፳፭ ቀን ፷፩ ዓ ም በመንበረ ፓትርያርኩ አዳራሽ ተደርጐ «ስብከትና የስብከተ ወንጌል መስፋፋት» በሚል

የውይይት ርእስ ስብከተ ወንጌል ማለት ማስተማርና ማስማር ነው ወይም በአጠቃላይ አነጋገርም ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መጥራትና የእግዚአብሔር ልጆች እንዲሆኑ በማስረዳትና በማስተማር መርዳት ነው በማለት ጉባኤው ተርጉሞ ፤

ስለዚህ ፤

፩/ ለዚህ ሥራ የሚመጥኑ ሰዎች ወይም ሰባክያን የሚባሉት አስቀድሞ በሙያው መሰል ጠንና መሠማራት እንዳለባቸው በሥራ ሲሠማሩም አስፈላጊው መመሪያ ተሰጥቶአቸው ተገቢው ቁጥጥር ርዳታና ማበረታት እንዲሁም ችግራቸውን መጠየቅ አስፈላጊ መሆን ፤ እንዳይዘነጋ ፤

፪/ መጀመሪያ በተማሩት ላይ እውቀት እየጨመሩ ጊዜውን ተከትለው ስብከተ ወንጌሉን ከምእመናኑ ኑሮ ጋር በማዛመድ እንዲያስፋፉ በየጊዜው የመሻሻያ ትምህርት መስጠት ዘመናዊ አሠራርና አፈጻጸም ስለሆነ እንዲታሰብበት ፤

፫/ ሰባክያን በደብር አለቆች የታወቁና የተደገፉ ሁነው በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ ወግና ሥነ ሥርዓት ባለው መልክ በሥራው እንዲሠለፉ ተገቢው ዝግጅትና ድርጅት ተሟልቶ አስፈላጊው ርዳታና መተዳደሪያ በምዕመናኑም ሆነ ከቤተ ክህነት እያገኙ ሐዋርያዊው አገልግሎታቸውን ከልብ እንዲፈጽሙ ማድረግ ማሻቱን ፤

፬/ ስብከትና ትምህርት ጊዜን ጠብቆ ሰዓት ለይቶ ፤ አጋጣሚን ተንተርሶ ስለሆነ ጠቅላላ መመሪያ በመስጠት የስብከቱን ጊዜና መጠን በሰርክና በነግህ እንደሚሆን አስቦ የቤተ ክርስቲያን ጸሎትና ሥርዓት ለሕዝቡ እንደሚያመች አዋሕዶ በማዘጋጀት ማቅረብ ማስፈለጉን ፤

፭/ በትልቁ የየክፍለ ሀገሩ የስብከተ ወንጌል ድርጅት እንዲኖርና ጠቅላላ ዓመታዊ ወይም የመንፈቅ ውይይት በማድረግ ስለቤተ ክርስቲያን አቋምና ስለኅብረተሰቡ ዝንባሌና ጊዜ አመጣሽ አስተሳሰብ እያጠኑ በስብከተ ወንጌል አማካይነት አብሮ ገብ የሚሆኑ ችግሮችን ለመቋቋምም ውይይት አድርጎ ውሳኔ በማሳለፍ ተግቶ ለመሥራት አገልግሎትን ይበልጥ ለማሻሻል አቋሙን ማጠንከር ፤ እንደሚገባ ፤

፮/ የወንጌል ልማት ወይም የልማት ወንጌል በሚለውም አስተሳሰብ በመመራት በኅብረተሰቡ የኑሮ ችግር ተካፋይ በመሆን ማኅበራዊአገልግሎት ለመስጠትና ርስ በርሱም እንዲረዳዳ በማድረግ ድንቁርና እንዲጠፋ ፣ ድህነት እንዲወገድ ፣ በሽታ እንዲቀነስ፣ ሥነ ሥርዓትንና ግብረገብን የተከተለ ኑሮ እንዳደረጅ በማሰብ በየሰንበቴውም ሆነ በየዓመት በዓላቱ ዕለት ከልማት ድርጅቶች ጋር ጭምር በመተባበር ለሃይማኖት ጽንዓት ፣ ለሀገር ብልጽግና ለትውልድ ጠቅላላ ደኅንነት አብልጦ በማሰብ ሐዋርያዊ ግዳጅን መፈጸም ማሻቱን አስገንዝቦ ፤ ጉባኤው አስፈጻሚ ክፍሉም የበኩሉን እንዳይዘነጋ አደራ ብሏል ።



የቤተ ክህነት ጠቅላላ አስተዳደር ጽ/ቤት የዚህን ድርጅት ጠቃሚነት በሚያውቀው መሠረት ሳይውል ሳያድር ርምጃ እንደሚወስድ የጉባኤውን ማሳሰቢያና ውሳኔዎች በሥራ እንዲገለጹ እንደሚያደርግ ተስፋ ተጥሎበታሎል ።

# የቤተ ክርስቲያን ርምጃ

ርምጃ ሲባል መንቀሳቀስን ያሳያል እንቅስቃሴ ሲባልም ባሉበት መውደቅ መነሣት መንፈራፈር አለና ርምጃ የሚባለው ቃል የሚያሳየው ወደፊት መግፋትን ፤ መጨመርን ነው ። በዚህም ወደፊቱ የሚገሰግሥ ሰው በሐሳብም በሥራም ከፍተኛ ውጤት ሊያስገኝ ይችላል ። ርምጃ በሁሉ ያለ ቢሆንም በተሰለፈበት የጦር ሜዳ አስቀድሞ ፤ ፈጥኖ ሰይፍ ጨብጦ ፤ የጠላቱን ቸብቸቦ ቆርጦ የድል ባለቤት ለመሆን ለሚፈልግ ወታደርና «እኔ ሩጫዬን ጨርሻለሁ ሃይማኖቴንም ጠብቄአለሁ እንግዲህ ወዲህ የውነት ፈራጅ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰጠኝን የድል አክሊል እጠብቃለሁ» እያለ ለሚመካ ሐዋርያ የግል ሀብት ነው ። ወታደርና ሓዋርያን በማነጻጸር ከጠቀስን ከሁለቱ ማንኛው መሥመሩን ጠብቆ ርምጃውን እንደቀጠለ ልንመለከት ይገባናል ። ሕዝብ በምድር ላይ መብዛት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ መሪ መሻቱ አልቀረም መሪውም ሕጉን የሚያስከብርለትን ይሻል ። ስለዚህም ነገሥታት ወይም ልዩ ልዩ የዓለም መሪዎች በወታደር ኃይል ሐሳባቸውን ስለሚያስፈጽሙ ሥርዓተ መንግሥት በዓለም እየተስፋፋ ይኖራል ። ፍቅር ወይም ጥላቻ በዓለም ውስጥ ቢኖሩም ግዛት እስከ አሁን መልኩን አልለወጠም ። በሐዋርያትም በኩል እግዚአብሔር ልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን በየጊዜው ይመርጣል ። ሥራቸውንና ትምህርታቸውን በተአምራት ያጸድቃል ። ግን እንዲህም ሆኖ በጠቅላላው የዓለም ይዞታ ላይ የቤተ ክርስቲያን ርምጃ እምብዛም ሲፋጠን አይታይም ። ጥቂት ዓመታት ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል ለዓለም ለማዳረስ የተፋጠነ ርምጃ አደርጋለች ። ከነዚያ ዓመታት ወዲህ ግን አንድ ሥፍራ ቆማ የቀረች ርምጃ ያቃታት ፤ መንቀሳቀስ የተሣናት መስላ ታይታለች ። ያደረገችው እንቅስቃሴም ራሷን በራሷ ለመከፋፈል፤ ለመነጣጠል እንጂ ከምሥራቅና ከምዕራብ ፤ ከሰሜንና ከደቡብ የሚመጡትን የእግዚአብሔርን ቤተሰብ ሰብስቦ አንድ ቤተ ክርስቲያን ለመሆን እስኪችሉ ድረስ ተገጣጥመው እንዲሠሩ ለማድረግ አላስቻላትም ። ይህም በመሆኑ ወደቤተ እግዚአብሔር ከገቡት ውጭ የቀሩት በዝተው ይታያሉ ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዓለም የክርስቲያኖች ይዞታ ላይ ልዩ ሥፍራ ይዛ ትኖራለች እውነተኛውን ሃይማኖት አለመግደፏ ፤ በትሕትና ደጅ መጥናቷ ፤ መልካም የሥነ ምግባር ፍሬ በብዛት ማበርከቷ እርምጃዋን አፋጥኖላታል ከክብር ወደ ክብር እንድትሸጋገር አድርጓታል ።

www.ethiopianorthodox.org

ይህ ዛሬ የምናከብረው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሆነው የተሾሙበት የሁለተኛው ዓመት መታሰቢያ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እድገት መጨመሩንና ርምጃው መፋጠኑን ያሳያል ። በበዓሉ ምክንያት በካህናትና በምእመናን በሊቃውንት አንድነት የተመሠረተው ጉባኤና ሥራው በጉባኤው የተደረጉ ንግግሮች ከውይይቱ የተገኘው ውሳኔ በጠቅላላው በበዓሉ ሥነ ሥርዓት ብዙውን ነገር አጉልተው ይመሰክራሉ ። ይህ አዲስ የሥራ መልክ እየዳበረ ይህ አዲስ ጉልበት እየጨመረ ከሄደ የቤተ ክርስቲያንም ርምጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄዱ አያጠራጥርም ።

በሥራ ላይ አንዳንድ ችግር ማጋጠሙ እውነት ነው ። ነገር ግን ሌሎችን ሠራተኞች ሲታዘቡ ሥራቸውንም ሲተቹ ኑሮ ራስ ሥራን በተረከቡ ጊዜ እጅን አጣምሮ እግርን አነባብሮ መታየት እጅግ በጣም አስደንጋጭና አሳፋሪ ነገር ነው ። እንግዲህ የቤተ ክርስቲያናችን ርምጃ እያደገና እየተፋጠነ ሄዶ ከዚህ ታላቅ ግብ ከደረሰ ተባብሮ መሥራት ፤ ከምእመናን ሁሉ የሚፈለግ የሥራ ግዴታ ነው ።

በመንፈሳዊ መንገድ ሕዝበ ክርስቲያንና ምእመናኑን አስተባብሮ መምራት የመንፈሳዊ አባቶች ኃላፊነትና ታላቅ ባለአደራነት በውነቱ በዚህ ባስቸኳይ የቤተ ክርስቲያን ርምጃ ላይ ሥራ የሚፈታና ሥራየሚያስፈታ ከታናናሾችም አንዱን የሚያስት ቢኖር ለእንደ ዚህ ያለው ሰው ከሕይወት ሞት ይሻለዋል ። ይህ ነገር ካህናትንም ምእመናንንም አይለይም ።

አንዲት ቤተ ክርስቲዳያን ካህናትም ምእመናንም ተገጣጥመው መሠረትና ጉልላት ጣራና ግድግዳ ሆነው የተሠሩላት ናትና በማንኛውም በኩል ስንፍና ቢገባ የቤተ ክርስቲያንን እድገት ይጐዳል ፤ ርምጃዋንም ይገታል እንግዲህ የቤተ ክርስቲያን ርምጃ እንዲጨምር ሁላችንም እንተባበር ። ይህም ሕግና ሥርዓቷን በማክበርና በመጠበቅ ተግባሯንና ትሩፋቷን በመፈጸም ሲሆን ኑሮአችንንም በእውነተኛ ክርስቲያን መሠረት ላይ በማጽናት ነው ።

# የንግግርና የመግለጫዎች አስተዋጽኦ

፩ኛ/ ቤተ ክርስቲያንና ሥርዓቷ ፤
፪ኛ/ ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ፤
፫ኛ/ ቤተ ክርስቲያንና ርምጃዋ በሚሉት ዐበይት ርእሶች መነሻ ልዩ ልዩ እውቀት ያላቸው አበውና ሊቃውንት እነዚህን ርእሶች ከሌላ ሐሳብ ፤ ጋር በማዋሐድ ከሚያዝያ ፳፮ ቀን ፷፬ ዓ/ም እስከ ሚያዝያ ፳፰ ቀን ቀን ፲፱፻፷፬ ዓ/ም ሰፊ መግለጫና ንግግር በጉባኤው ላይ አሰምተዋል ።

የመግለጫውና የንግግራቸው ፍሬ ነገር ባጭር ባጭሩ በሚከተለው ሁኔታ ቀርቧል።

፩/ ቤተ ክርስቲያንና ሥርዓቷ ፣

ሀ/ " ቤተ ክርስቲያንናሥርዓቷ " በሚለው ርእስ አለቃ አያሌው ታምሩ ከሰጡት ሰፊ ማብራሪያ ባጭሩ የተውጣጣ /

" ቤተ ክርስቲያን ሲባል ማደሪያውንና ተሰብሳቢውን ነው ። ቤተ ክርስቲያን ዓባሎችዋ የበዙ የክርስቶስ አካል ናት፤ የክርስቶስ ሙሽራ ናት። ሙሽሮቹ ሲለያዩ ኑሮ እንደ



ሌለ ሁሉ ቤተ ክርስቲያንም ከክርስቶስ መለየት አትችልም። ቤተ ክርስቲያን የራስዋ ሥርዓት አላት እነሱም ፣

፩ኛ/ ለአሠራሯና አቀማመጥዋ ፤
፪ኛ/ የጸሎት ሥነ ሥርዓት ፤
፫ኛ/ የምትመራበትና የምትተዳደርበት ሥርዓት ፤
፬ኛ/ በሃይማኖት የተመሠረተ የኑሮ ሥርዓት ፤
፭ኛ/ የራስዋ የትምህርት ሥነ ሥርዓት ናቸው

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምልክት እግዚአብሔር መሆኑን ዳዊት "እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች ይላል" መታዘዝ ፤ ማዘዝ ፤ መመጽወት ፤ መከባበር ፤ የመሳሰሉት የእግዚአብሔር ሥርዓቶች ናቸው ። ግን አሁን እየጠፉ መሄዳቸው ነው ።

፮ኛ/ ካህናት ተግባራቸው አገልግሎት እንጂ የተገልጋይነት መንፈስ ሊኖራቸው አይገባም ። ክብርን ለመጠበቅ ሲባል ብዙ መንቃቀፍ ስለሚከተል መለያየትን ያመጣል ።

፯ኛ/ የኛ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር የምትመሳሰለው በአንድ አምላክ በማመን ሲሆን አብ ፤ ወልድ ፤ መንፈስ ቅዱስ በማለትና የሥላሴን ምሥጢር በመመርመር ትለያለች ቤተ ክርስቲያን የራስዋ አሠራር ፤ አመራርና የውስጥ ደንብ አላት ። አስተዳዳሪዎችም ከጳጳስ እስከ ዲያቆን ያለው ምልክት አለው ። እያንዳንዱ ክርስቲያን የግልና ማኅበራዊ የሆነ የጸሎት ሥርዓት አለው ። ሕፃናትን ማስተማር የቤተ ክርስቲያን ተግባሯ ነበር ፤ ነውም ። ይህ በሃይማኖትና በኑሮ ሥርዓት እንዲመራ የመምህራን ድካም ከፍተኛ ነው ። ይህ የቤተ ክርስቲያን አደራ የሚጠበቀው ሕዝቡ በኅብረት ሲደግፉት ነው ።

ለ/ ቤተ ክርስቲያንና ሥርዓቷ(ታሪኩና አመጣጡ) ፣

ዶክተር ሥርግው ሀ/ሥላሴ ከሰጡት መግለጫ የተውጣጣ

"ቤተ ክርስቲያን የሥነ ጽሑፍ የጸሎት ባህል ታወርሳለች ፤ ዛሬ እንደምናየው ቤተ ክርስቲያን እንደዘመኑ መለወጥ አለባት ። ሥርዓቱ ሁሉ ቀድሞ ሐዋርያት ፤ ከዚያም ወዲህ አበው ያወጡት ስለሆነ ሊሻሻል ይችላል ፤ ግን የሚለወጠው ከሕዝቡ የመጣ ሕዝቡ የሚከተለውና የሚቀበለው ሲሆን ነው ። ቀደም ሲል በነፍሬምናጦስ በ፬ኙ (በተሰዓቱ) ቅዱሳን መምጣት አማካይነት ጥቂት ለወጥ ተደርጓል ። በ፲፫ኛው መቶ ዓመት የጳጳስነትና የእጨጌነት ሥልጣን ተመሠረተ ሲሶ መንግሥት የተባለው ያኔ ተጀመረ ግን ከየቱ ክፍል ያለው ግዛት እንደሆነአልተለየም።ለቤተ ክርስቲያን ክብርና የትምህርት ሥርዓት ማዕረግ ፤ የካህናት ተግባር በዓዔ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን የተወሰነ ጸሎትም ከበስመ አብ እስከ ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም ነበረ ።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የምእመናን ችግር ማቃለል ፤ ወንጌልን ማስተማር ከክርስቶስ የተሰጣቸው ሥርዓትና ትእዛዝ ነው ። ግን ይህ ትእዛዝ የሚከተለው ስላጣ አረማውያን ሊበርከቱ ችለዋል ። የኢትዮጵያም ነገሥታት ክርስቲያኖች በመሆናቸው ለካህናት ድሎትን ስለሰጡ ወንጌል በሚገባ አልተሰበከችም ፤ ቤተ ክርስቲያንንም የመንግሥት ጥገኛ አድርገዋታል ።

www.ethiopianorthodox.org

ከእንግዲህ ግን ለካህናት ፤ ለዲያቆናት ፤ ለምእመናን መመሪያ ማዘጋጀት ይኖርብናል፡

— ነዳያንን መርዳት ፤ ራሳቸውን የሚያስተዳድሩበትን ድርጅት ማቋቋም፡
— ወጣቶችን በሙያ ማሠልጠን ፤
— በኤኮኖሚ ፤ በሶሺያልና በልማት ሥራዎች መተባበር ፤
— የቤተ ክርስቲያን ገዳማትና ሥነ ሥርዓት አለመሻሻሉ ሁሉም እንደ ነበረ ነው ።
— ቤተ ክርስቲያንን የመንግሥት ጥገኛ አድርገዋት የኖሩ አበው ናቸው።

<u>ልንሻሻል ያልቻልንበት ፡</u>

፩ኛ/ የራሳችን ጳጳስ ስላልነበረን ፤
፪ኛ/ እኛ የያዝነውን የማንለቅ ስለሆንን ፤ የመጀመሪያውን ስለማንለቅ ፤ ለምሳሌ ፤ (አጽዋማት)

ያሻሻልነው ፡

፩ኛ/ የራሳችን ጳጳሳት መሾማቸውና መኖራቸው ፤
፪ኛ/ የቋንቋ መግባባት መፈጠሩ ፤
፫ኛ/ የአንዳንድ ሥነ ሥርዓት መሻሻልና መስፋፋት ፤
፬ኛ/ የመጻሕፍትና የስብከት ዘዴ መስፋፋት ፤
፭ኛ/ ነዳያንን መርዳት፤ካህናትን ማሠልጠን የቤተ ክርስቲያን ተቀዳሚ ተግባሮች ሆነው መቈጠር ናቸው ።

፪/ <u>ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ፡</u>

ሀ/ « ምእመናንና ቤተ ክርስቲያን »

አቡነ ሳሙኤል (አባ ገብረ እግዚአብሔር ደገ)

ካሰሙት መግለጫ ባጭሩ የተውጣጣ ፤

"የቤተ ክርስቲያን ትልቅነት የሚታወቀው ክርስቶስ ያደረገላትን ሁሉ ለማስታወስ ከቻልን ነው።ቤተ ክርስቲያንንና ምእመናንንለማስተባበር እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ እንሞክር ።

፩ኛ/ ቤተ ክርስቲያን የጎደላትንና የሚያስፈልጋትን ለይተን እናውቃለን ወይ ?

፪ኛ/ የየአንዳንዱ ዓባል ግዴታ ለቤተ ክርስቲያን ምንድነው ?
፫ኛ/ በግዴታችን መሠረት ትምህርታችንን ፤ ባህላችንንና መጻሕፍታችንን በምን ዓይነት ዘዴ አዋሕደን ለስብከት ማቅረብ አለብን ?



"ቤተ ክርስቲያን ማለት ለዲያቆን ፤ ለቄስ ፤ ለመነኩሴ ብቻ ሳትሆን ለመላው ሕዝበ ክርስቲያን ናት መሠረቷም ፍቅር ነው ። ፍቅ ርም ክርስቶስን የምናይበት መሣሪያ ነው ።



ብፁዕ አቡነ ሣሙኤል ንግግር ሲያደርጉ

የቤተ ክርስቲያንና የምእመናን ግንኙነት ምሥጢሩ በጣም ጠለቅ ያለና ለመመርመርም የሚያዳግት ስለሆነ እያንዳንዱ ዓባል በራሱ ተግባር የሚገልጠው ነው ።"

ለ/ «ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን» ፤

የተከበሩ አቶ አክሊሉ አጥላባቸው ካደረጉት ንግግር የተውጣጣ

"ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን አካለ ሥጋና አካለ ነፍስ ናቸው ። አንዱ ያለ ሌላው የሞተ ነው ። ቤተ ክርስቲያን በጥምቀት ወልዳ የሥላሴ ልጆች ያደረገችን እናታችን ናት ።

www.ethiopianorthodox.org

እንደ እናትነቷም የጽድቅን ምግብና መጠጥ ትመግባለች ።”

ምእመናን የእናታቸውን ቤት ይሠራሉ ፤ ይጠብቃሉ፤ ያገለግላሉ ዘወትር ጥዋትና ማታ ይጎበኙዋታል ከወንበዴም ይከላከሉላታል ። ሁለቱም የሚገናኙት በዚህ ከሆነ ዛሬ ቸልተኝነት የተፈጠረው በእናቲቱ ወይስ በልጆችዋ? እንደእውነቱ ከሆነ ጥፋቱ በሁለቱም በኩል እጅግ ጎልቶ ይታያል ። አንዱ በሚገባ አያቀርብም ሌላው ደግሞ ለመቅረብ ሙከራ አላሳየም።አሁን ግን የሚያስፈልገው ባለን አቅም ቤተ ክርስቲያንን ልንከባከባት እስዋም እናታዊ አገልግሎቷን እንዳታቋርጥብን ጥፋታችንን ርስ በርሳችን ተራርመን ወደፊት መራመድ ነው ።



የተከበሩ አቶ አክሊሉ አጥላባቸው በጉባኤው ላይ ንግግር ሲያደርጉ ።



ሐ/ ቤተ ክርስቲያንና ወጣቶችዋ ፤

የተከበሩ አቶ ሠይፈ ታደሰ ፤

ካደረጉት ሰፊ ንግግር የተውጣጣ ፤

“ለአንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመታት ያህል በውጭ አገር መነኮሳት ስትመራ ቆይታ ዛሬ የራስዋን ፓትርያርክ ራስዋ ለመሾም መቻሏ የቤተ ክርስቲያንንና የምእመናንን የመሻሻል ታሪክ አጉልቶ ያሳያል ።

ቤተ ክርስቲያን ስንል ሕንጻውን ብቻ ማለታችን ሳይሆን በአጭሩ አገልጋዮችዋንም ይጨምራል ። ምእመናን ስንልም የአንድ አገር ሕዝብ ማለታችን ሳይሆን ከዜግነቱ ሌላ በአብ በወልድ ፤ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቆ የወልድን አዳኝነት አምኖ የአንዲት ኦርቶዶክሳዊትቤተ ክርስቲያን ዓባል መሆኑን የሚገልጽ ነው ።

ቤተ ክርስቲያን የወንጌል ስብከት እንዲስፋፋ ፤ የክርስቶስ ቤተ ሰቦች እንዲበዙና ሰላም እንዲሰፍን ከፈጠረው ተለያይቶ ለሞተና ለሞት የተዘጋጀውን ወደ ፈጣሪው የሚመለስበትን መንገድ በማሳየት የምታስታርቅ ወላጅ እናት ናት ። ስለልጆቿ ብዙ መንከባከብ ማድረጓን የሚያውቁ ውለታ ተቀባዮች ቢኖሩም የማያውቁላትም አልታጡም ። ቤተ ክርስቲያን ራስዋን ልታሻሽልበት ብትፈልግ የምትመራበት መሠረት አለን ? ብንል ዘመኑና ሁኔታውን ተከትሎ በመሥራት የታወቀውን የቅዱስ ጳውሎስን ዘዴ መከተል ይበቃል ። ይህ ለምን ተወሰነ ? ያ ከየት መጣ ? የሚለውን ትውልድ ቅዱሳት መጻሕፍትን መመሪያ አድርጋ ብታስተምር ወጣቶች ቤተ ክርስቲያንን በመቅረብ ዓባሎችዋ ይበዙ ነበር።ያለፉት ምእመናን ቤተ ክርስቲያን የምትሰጠውን ትምህርት ያለምንም ምርምርና ጥያቄ በእምነት ብቻ የሚቀበል ስለሆኑ የቤተ ክርስቲያን ታዛገሮችና ተገገርዎች ስለነበሩ በሃይማኖት መሪዎች ላይ ችግሩ እምብዛም እንዳልጠነከረ ይነገራል ፤ ዛሬ ግን የመጠየቅና የመመርመር ጊዜ ስለሆነ በኑሮው የሚገጥመውን ማንኛውንም ጉዳይ ራሱ በጥረቱ ለማቃለል ሲጥር ቤተ ክርስቲያን ግን በዘመናዊ መሳሪያና በሠለጠኑ ሰዎች መጠቀም እንዳለባት የምትረዳበት ጊዜ አልዘገየም ። በዚህም ምክንያት ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ተለያይተው መኖር እንደማይችሉ በመገንዘብ ሕዝበ ክርስቲያኑ በየቦታው እየተሰበሰበ ሲወያይ ይታያል ። በልዩ ልዩ አቋም የደረጃ የልዩ ልዩ እምነቶች በተነሡበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያንይህን የገጠማትን ውድድር ለመቋቋም በተጠና ዘዴ መነሣትግዴታዋ ይሆናል ። የቤተ ክርስቲያን ግድግዳ የሆነውን ወጣቱን በበለጠ ለማቅረብ የሚችለው ሲሞቱ በነፍስ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ችግር ደጋግሞ በመግለጽ ብቻ ሳይሆን በዕለት ኑሮ ላይ የሚያጋጥሙትን የምድር ፕሮብሌሞች ለመፍታት ቤተ ክርስቲያን በተቻላት ተካፋይ ሆኗ ስትገኝለት ነው ።”

መ/ ወጣቶችና ቤተ ክርስቲያን ፤

አቶ አግደው ረዴ ፤
ከሰጡት መግለጫ የተውጣጣ ፤

“ወጣት የምለው ከ፲፪—፳፭ ዓመት ክልል ውስጥ ያለ ነው። መንፈሱ ትኩስ በቀላሉ የሚርቅና የሚቀርብ፤ለሥራ የታጠቀ ነው።በሀገራችን ስለ ወጣቶች በትምህርት መጎልመስ የተሞከረ ቢሆንም የመንግሥቱን ያህል ቤተ ክርስቲያን ተጨምራየመንፈስን ጥማት

www.ethiopianorthodox.org

ለማርካት አልተቻለም ። ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ማኅበር እየመሠረቱ መዲረባቸው ሊደነቅ ይገባል ። ቤተ ክርስቲያን ወጣቱን በሃይማኖትና በባህሉ ኮርቶ እንቅኖር ማድረግ አለባት ። ወጣቶች እንዲያገለግሉና እንዲገለገሉ ለማድረግ የተማሩ ሰዎችን ቀጥሮ ማሰማራት ፤ ጊዜውን የተከተለ ትምህርት መስጠት ፤ ከወላጆች ጋር በመ



መምህር ሰሎሞን ገብረ ሥላሴ ለጉባኤው መግለጫ ሲሰጡ

ተባበር ስለወጣቶች አስተዳደግ ማቀድ በአንዳንድ የኅብረተ ሰብእን አቀዋም በሚበላሹ አካባቢዎች ለመገኘት ቤተ ክርስቲያን የዕድሜ ገደብ ሕግ ብታወጣ ጥሩ ነው ።"

፫ኛ/ " ቤተ ክርስቲያንና ርምጃዋ ፡ (ልማት)

አቶ ጌታነህ ቦጋለ ፤

ከሰጡት ማብራሪያና መግለጫ የተውጣጣ

"የቤተ ክርስቲያን ርምጃ አመጣጥ ክርስቶስና ሐዋርያት ይፈጽሙት በነበረው ላይ የተመሠረተ ነው ። በዚህ አኳያ ጳጳሳት የክርስቶስ፤ ካህናት የሐዋርያት ምሳሌዎች ናቸው እንግዲህ እንደ ኢትዮጵያ እምነት አጀማመር ጳጳሳትና ካህናት የተሰጣቸውን ሥራ ቢያከናውኑ ኖሮ እንኳን በአገራችን በመላው አፍሪካ አረመኔ አይገኝም ነበር ። ሚሲዮናውያን የሠሯቸውን ት/ቤቶችና ሆስፒታሎች ከዳር ቁመን ከማድነቅ እንድን ነበር ።

አሁን እንደምንመለከተው ቤተ ክርስቲያንን የሚጠቀሙባት እውነተኞች አገልጋዮች ሳይሆኑ ማደሪያ ፤ መጣጊያና ማዳጊያ ያጡ ስንፖች ስብከቱ ቀዘቀዘ ወንጌሉ ተረሳ ።



ከ፩ሺህ፮፻ ዓመታት በፊት የነበሩ ነገሥታት ክርስቲያኖች ስለ ነበሩ ለቤተ ክርስቲያን ተፈላጊውን ሁሉ ስለሚያደርጉ ጉዞው የተቃና ነበር ። ካህናቱንም በማክበር በገዢነት ፤ በአፈ ንጉሥነት በመኰንንነት ማዕረግ ያስቀመጡዋቸው ስለነበር ክብር መስሏቸው እየዞሩ ማስተማርን ቸል ብለውት ነበር ። ይህ ይዞታ ለጊዜው ለካህናቱ ይመች እንጂ ቤተ ክርስቲያንን ግን የመንግሥት ጥገኛ አድርጓት ቀርቷል ። የተማሩት ካህናትና ጨዋው ግኙኝነታቸው የጌታና የሎሌ ስለነበር ትምህርት ሰጪ አልነበረም ። አሁን የካህናት ባለሥልጣን አለመሆን ለቤተ ክርስቲያን መድኅን ይሆን ? ግን አሁንም አንድነቱ ገና የሚጠበቅ ነው ። ቤተ ክርስቲያን በስብከት ፤ በወጣቶች መንፈሳዊ አገልግሎት በልማት መልካም ርምጃ ማሳየት ጀምራለች ።"

የልማት ኮሚሽን ዓላማ ፡

፩ኛ/ ለነዳያን ራሳቸው ሠርተው የሚረዱበትን ድርጅት ማቋቋም ፤
፪ኛ/ ወጣቶችን ለሙያ ትምህርት ማሠልጠን ፤
፫ኛ/ ከመንግሥትና ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ተባብሮ መሥራት ነው ።

ትምህርት የልማት ሁሉ ፊታውራሪ በመሆን የልማቱ ሥራ መጀመሪያ አድርገነዋል ። ካህናቱም ዓላማውን ለሕዝቡ እንዲያስረዱ አደራ እንላለን ።

በቤተ ክርስቲያንና ርምጃዋ የወጣቶች ተካፋይነት ፡

ከአቶ ሰሎሞን ጅሩ ፤

ማብራሪያ ባጭሩ የወጣ ፤

" መጻሕፍት እንደሚነግሩንና እኛም እንደምናምነው ጳጳሳትና ካህናት የክርስቶስን መንጋዎች ካልጠበቁ "መካሪ የሌለው አገር የባለጌዎች ሠፈር ይሆናል" እንደሚባለው ነው ። የዲፕሎማሲ ኑሮን ካህናት የሚጠቀሙበት ከሆነ አፋቸው ይዘጋል ። ይህም ለሁለት ጌታ መገዛት ስለማይቻል የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውድቀት ያስከትላል ። ፍርሃት የውድቀት ዋዜማ ነውና ።

ሀ/ ቤተ ክርስቲያን ለወጣቱ ፡

፩ኛ/ በትምህርትና በሃይማኖት አንፃር መሰብሰብ ፤
፪ኛ/ ያለውን የገንዘብና የሰው ኃይል አንድነት አስተባብሮ መሥራት ፤
፫ኛ/ የመንፈሳዊ ትምህርት አሰጣጥ የሚሰበሰብ እንጂ የሚበተን እንዳይሆን አድርጋ ማዘጋጀት ፤
፬ኛ/ ለሕዝቡ ራሱን የማስቻል ትምህርት መስጠት ፤
፭ኛ/ መምህራን በግብር መምህራን ሆነው መገኘት ፤

ለ/ ከወጣቱ የሚጠበቀው ፤

፩ኛ/ ካህናትን በሥልጣናቸውና በአባትነታቸው ማክበር ፤
፪ኛ/ ከቤተ ክርስቲያን ጋር በቅርብ ተገናኝቶ መሥራት ፤
፫ኛ/ በተሰጣቸው ትምህርት መልካም ሥራ መፈጸም ፤
፬ኛ/ በሰንበት ት/ቤት ስለወንጌል መስፋፋት መጣርና የመሳሰሉት ናቸው

www.ethiopianorthodox.org

# ጋዜጦች ስለበዓለ ሢመቱ በርእሰ አንቀጻቸው ያሠፈሩት ሐተታ ፤

የብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያን በዓለ ሢመት ምክንያት በማድረግ ስለተፈጸመው ታላቅ የቤተ ክርስትያን ሹመት ስነ ሥርዓትና በዚሁም ሰሞን ስለተከናወነው ከፍተኛ የምእመናን ፤ የሊቃውንትና የካህናት ጉባኤ ጋዜጦች በተራ ዓምዳቸው ካሰፈሯቸው ሐተታዎች ሌላ በየርእሰ አንቀጻቸው በሰፊው አትተዋል ።

የአዲስ ዘመን ጋዜጣግ ንቦት ፪ ቀን ፲፱፻፷፬ ዓ ም ባወጣው ርእሰ አንቀጹ እንዲህ ሲል ጽፏል ።

“ <u>የመንፈሳዊ ነጻነት ዓውደ ዓመት</u> ”

«ብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ ርእስ ሊቃነ ጳጳሳት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ሁነው የተሾሙበት የመጀመሪያው ዓመት መታሰቢያ ትናንት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፤ ልዑላን ንጉሣዉያን ቤተሰብንአስከትለው በተገኙበት በመንበረ ፓትርያርኩ ቅፅር ግቢ በምትገኘው በቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስትያን በመንፈሳዊ ስነ ሥርዓት ተከብሯል ።

ሥጋዊውን የነጻነት ድል በዓል ተከትሎ የተገኘው ይህ መንፈሳዊ የነጻነት ድል በዓል ባለፈው ዓመት ግንቦት አንድ ቀን እጅግ ከፍ ባለ ስነ ሥርዓት መከበሩ ይታወሳል። ይህ መንፈሳዊ የነጻነት በዓል በኢትዮጵያ ቤተ ክርስትያን ታሪክ ውስጥ ያለፈውን የታሪክ ዓምድ ይዞ ሲነበብ ይኖራል ። ከሥጋዊው ድል ጋር መንፈሳዊው ድል ተጣምሮ ይከበራል ።ይህም ለመላ ኢትዮጵያ ምእመናን ትምክሕትና ኩራት ሁኖ ሲታሰብ ይኖራል ።

የክርስትያን ደሴት በመባል የታወቀችው ኢትዮጵያ ለብዙ ዘመናት ያህል ከወገኖቿ መምህራን መካከል ጳጳስ እንዳትሾም የመንፈሳዊ ነጻነት ሥልጣን መብት ተነፍጋ ሥልጣነ ክህነትን የሚያድል የባዕድ አገር ሊቀጳጳስ እያስመጣች መኖሯ አይዘነጋም ። የኢትዮጵያ ነገሥታት ከብዙ ዘመናት ጀምሮ ፤ የኢትዮጵያን ወሰንና ድንበር አስከብረው ነጻነቷን አስጠብቀውበክብር ማቆየታቸው ቢታወቅም ሥጋዊ ነጻነት ያለ መንፈሳዊ ነጻነት የተሟላ አለመሆኑን አርቆ በመመልከት የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት የአስተዳደር ይዞታ የተሟላ ሁኖ እንዲገኝ በየጊዜው ጥረትና ሙከራ ሳያደርጉ ያለፉበት ዘመን የለም ። ይሁን እንጂ ሙከራና ጥረታቸው ሳይሳካ ይኸን የዛሬውን የኢቶዮጵያ ቤተ ክርስትያን መንፈሳዊ ነጻነትና እድገት ሳያዩ አልፈዋል ። የኢትዮጵያ የቤተ መንግሥቱና የቤተክህነቱ ከፍተኛ ባለአደራዎችና መብት አስከባሪዎች ነገሥታቱ እንደመሆናቸው መጠን ፤ ምን ጊዜም ቢሆን መንፈሳዊ ነጻነትና ሥጋዊ ነጻነት ከነሙሉ መብቱ ፤ እንዳይጓደል የሥራ ዓላማቸው ፤ መንግሥታዊ አመራራቸው በዚሁ ጽኑ መሠረት ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ፤ ጊዜውን እየጠበቀ በየጊዜው ከመፈጸም አልተገታም ። ይሁን እንጂ ድሉና ዕድሉ ሊገኝ የተቻለው ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ነው ። በተለየም። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የመንፈሳዊ ነጻነትን ሥልጣንና መብት ለማስገኘት ግርማዊ ጃንሆይ ገና አልጋወራሽ ሳሉ ኤውሮፓን ሊጎበኙ በሄዱበት ወቅት በጊዜው ከነበሩ የእስክንድርያው ፓትርያርክ ጋር ስለኢትዮጵያ ቤተ ክርስትያን መንፈሳዊ ነጻነት የቀረቡት ጥያቄዎች ተደማጭነት ሳያገኙ ክርክሩም በትዕግሥት ተይዞ ሁለቱን ወገኖች በማያቃቅር ይዞታ ሁኖ መቆየቱ አይካድም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስትያን ትዕግሥትና ይሉኝታ የተደገፈ በመሆኑ ይህም ትዕ

www.ethiopianorthodox.org

ግሥት በሌሎቹ ዘንድ እንደ አላዋቂና ጭቆናው እንዳልተሰማት በመገመቱመላው የኢትዮጵያ ምእመናን መንፈሳዊ ነጻነትን ለማስገኘት መንፈሳዊ እንቅስቃሴ አደረጉ በዚህም ምክንያት ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ንጉሥ በተባሉ በአሥረኛው ወር በሰኔ ወር አራት ኢትዮጵያውያን መምህራን ለጵጵስና ተመርጠው ካንድ ግብፃዊ ሊቀ ጳጳሳት ጋር ተሾሙ ። ይህም የመጀመሪያው የመንፈስ ነጻነት ድል በኢትዮጵያ ጮራውን ፈነጠቀ ። በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ብርታትና ትጋት የቤተ ክህነት የነጻነት ዕድል በር ተከፈተ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በየጊዜው በተደረገው ራስን የመቻል ትግል ሙሉ የመንፈሳዊ ሥልጣን መብት በመቀዳጀት ኢትዮጵያ ከወገኖችዋ ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ለመሾም በቃች ። በኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ ፤ ኢትዮጵያውያን ሊቃነ ጳጳሳት በመሾም በቁጠባ ተይዞባት የነበረውን ሥልጣነ ክህነት ለመላ ኢትዮጵያ ለመናኘት መንፈሳዊ ዕድሏ ተቃናላት ። ስለዚህ ይህን መንፈሳዊ የነጻነት ዓውደ ዓመት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲያከብር መንፈሳዊ ኩራት እየተሰማው ነው » ።

እንዲሁም ዜና ቤተ ክርስቲያን የተባለው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተጠባባቂነት በየሳምንቱ የሚታተመው ቀጥሎ የተመለከተውን ግንቦት ፲፱ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም በርእሰ አንቀጽ በጻፈው የበዓሉን መዘክርነት አውስቶ ስለ በዓሉና ስለ ጉባኤው የሚከተለውን አስፍሯል ። ጽሑፉ ያተኮረው ምእመናንና ቤተ ክርስቲያን በሚለው ርእስ ላይ ነው ።

## «ምእመናንና ቤተ ክርስቲያን»

«ምእመናን ባልን ጊዜ በክርስቶስ ያመኑትንና የተጠመቁትን ቤተ ሰቦች ማመልከታችንነው ፤ የእምነትና የጥምቀት ምንጭም ቤተ ክርስቲያን በመሆኗ የምእመናን ትርጉም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለ ሲሆን የቤተ ክርስቲያንም ትርጉም በምእመናን ውስጥ ይገኛል ማለት ነው ። ቤተ ክርስቲያን የምእመናን መሠረት ስትሆን ምእመናምን የቤተ ክርስቲያን ጣራና ግድግዳ ናቸው፤ መሠረት ኖሮት ጣራና ግድግዳ ከሌሉት ጣራና ግድግዳ ቢኖሩትም መሠረት ከሌለው አንድ ቤት ቤት ሊባልና ሊጠቅም እንደማይችል ሁሉ ምእመናን ያለቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያንም ያለ ምእመናን ጥቅም የላቸውም።

የቤተ ክርስቲያን ብርሃን በመላው ዓለም ሊደርስ የሚችለው ምእመናንና ቤተ ክርስቲያን ሰምና ፈትል ሆነው ሲገኙ ነው ። የምእመናንና የቤተ ክርስቲያን ህልውና መታወቅ ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ ይብዛም ይነስም በምእመናንና በቤተ ክርስቲያን መካከል አንዳንድ ችግር ሲፈጠር መኖሩን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል ፤ ሆኖም የምእመናንን ችግር ቤተ ክርስቲያን ፤ የቤተ ክርስቲያንን ችግር ደግሞ ምእመናንን እያስወገዱ እስከ አሁን ድረስ ምእመናንና ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወት ተሳስረው ለመኖር ችለዋል ። ወደፊትም በዚህ ዓይነት መኖር ይገባቸዋል ።

ቤተ ክርስቲያን የምእመናንን ምእመናንም የቤተ ክርስቲያንን መሆናቸው ከታወቀ ዘንድ ቤተ ክርስቲያን የምእመናንን ችግር ለማወቅና ለማቃለል የምትችለው ምእመናን የቤተ ክርስቲያንን ችግር አውቀው ሲገኙ ነው ።

ቤተ ክርስቲያን በብሔራዊ ኅብረተ ሰብእም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የደረሰባትን ችግር ለምእመናን ገልጻ ካላስረዳች “ በሽታውን የደበቀ መድኃኒት አይገኝለትም ” እንደሚባለው ሁሉ ለችግሯ መፍትሔ ለማግኘት አትችልም ምእመናንም ከቤተ ክርስቲያን የተሠወረውን ውስጣዊ ችግር ለቤተ ክርስቲያን ገልጸው ካላስረዱ ውስጥ ውስጡን የሞራል ድቀት እንደሚደርስባቸው ግልጽ ነው ፤ የሞራል ድቀት ከደረሰበትም ሕዝብ የኤኮኖሚና የጉልበት ድቀት የደረሰበት ሕዝብ ፈጥኖ ይነሣል ። በአንድ አገር ላይ የሚደርሰውን የሞራል ድቀት ከሥሩ ነቅሎ ለማጥፋት የምእመናንና የቤተ ክርስቲያን ኅብረት ፍቱን መድኃኒት ነው። በዚህ ረገድ የብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስን የሁለተኛ ዓመት የፓትርያርክነት በዓለ ሢመት ምክንያት በማድረግ ባለፈው ሳምንመ ከሚያዝያ ፳፰ ቀን እስከ ሚያዝያ ፴ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም ድረስ አምስት ቀን ያህል ስለቤተ ክርስቲያን ትምህርትና ሥርዓት መሻሻል ጉዳይ በመንበረ ፓትርያርኩ የተደረገው የካህናትና የምእመናን ጉባኤ እጅግ በጣም የሚያስመሰግንና ለቤተ ክርስቲያን የወደፊት ርምጃ ተስፋ የሚጣልበት ነው ።



ይህ በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ዘመናዊ አመራርና ልዩ የአስተዳደር ችሎታ ለመጀመሪያ ጊዜ በካህናትና በምእመናን መካከል የተደረገው ጉባኤ የሚያቀርበው አሳብና የሚያወጣው የማሻሻያ ደንብ ለዋናው የኢትዮጵያ ቅዱስ ሲኖዶስ የሚጠቅምና የቤተ ክርስቲያንን የወደፊት ርምጃ የሚያፋጥን ስለሆነ በየዓመቱ የማያቋርጥ ቢሆን የሚደገፍ ዓላማ ነው ። ለመጀመሪያ ጊዜ በተደረገው በአሁኑ ስብሰባም ቢሆን ለቤተ ክርስቲያን ትምህርትና ስነ ሥርዓት መሻሻል ይጠቅማሉ ተብለው ለብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩና ለቅዱስ ሲኖዶስ የቀረቡት ሐሳቦች እጅግ በጣም ጠቃሚዎች ሆነው ተገኝተዋል፤ይህ ጉባኤ የዘመኑ ምሁራን ስለሚገኙበት በሚያቀርበው ሐሳብና በሚያወጣው ረቂቅ ዋናው የኢትዮጵያ ቅዱስ ሲኖዶስ ታላቅ ድጋፍ እደሚያገኝና የኢትጵያ ኦርቶዶክስ ሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንም መንፈሳዊ ርምጃ ያማረና የተፋጠነ እንደሚሆን ታምኖበታል፤ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም የመጀመሪያው የመሻሻል ምልክት ስለሆነ ለኢትዮጵያውያን ምእመናን ሁሉ ታላቅ የምሥራች ነው ።»

www.ethiopianorthodox.org